# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 023 መስከረም 23 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!











ምትኩ ደስታ



ሀደ ሲንቄ ሹካሬ ቦረና



በዳዳ ጂማ



ወይዘሪት ፋዩ ተማም

ፎቶ - ገበየ ገብሬ

# ኢሬቻ ትውፊቱን ሳይለቅ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ የበዓሉ ተሳታፊዎች አሳሰቡ

- የኢሬቻ በዓል በሆረ-ሀርሰዴ ተከብሯል

ገጽ 4








«ኃያሳን ሀገራት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና የሕዝቡን ተፈጥሯዊ የመወሰን መብት ማክበር ይገባቸዋል»

## «ኃያሳን ሀገራት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና የሕዝቡን ተፈጥሯዊ የመወሰን መብት ማክበር ይገባቸዋል»

- የኩባ አምባሳደር ሆርጌ ሌፌብሬ ኒኮላስ

ዘሳለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ኃያላን ሀገራት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና የህዝቡን ተፈጥሯዊ የመወሰን መብት ማክበር እንደሚገባቸው የኩባ አምባሳደር ሆርጌ ሌፌብሬ ኒኮላስ

«ኃያሳን ሀገራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የፈተና ሥርዓቱ መቀየሩ ስርቆትና ውኸንብርን ለመከላከል ያስችላል

ዘሳለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና ጣቢያ ሥርዓት የተቀየረው አንድን አካባቢ ለመጥቀም ታስቦ የሚደረገውን አካሄድ ለመከላከል እና የፈተና ስርቆትና ውኽንብርን በመከላከል ተማሪዎች ተረጋግተው እንዲፈተኑ ለማስቻል መሆኑን የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ ገለጹ።

ዶክተር ፋንታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የፈተና ጣቢያ ይሰጥበት የነበረው አሰራር ተቀይሮ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲፈተኑ የተወሰነው፤ተማሪዎች ከሐሰተኛ መረጃዎች፣ ከሐሰተኛ መልሶች እና ከሐሰተኛ የፈተና ወረቀቶች ራሳቸውን ጠብቀው ተረጋግተው እንዲፈተኑ ለማስቻል ነው።

ፈተና እንዳይሰረቅ በጉዞም ሆነ በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ ባሉ እንቅስቃሴዎች ጥብቅ ቁጥጥር ይካሄዳል ያሉት ዶክተር ፋንታ፤ ፈተና አውጥተናል የሚሉ አካላት በማህበራዊ ሚዲያ እየለቀቁ ተማሪዎቹ ለቀጣይ ቀን እንዳይዘጋጁ በመረበሽ ውጤታቸውን ለማበላሸት የሚያደርጉትን ጥረት ለማስወገድ ሲባል ዩኒቨርሲቲዎች



ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ

ውስጥ ምንም አይነት የዲጂታል መሳሪያዎች አይኖሩም ብለዋል።

ተማሪዎች ምንም አይነት የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ማሳለፍ አይችሉም። ተንቀሳቃሽ ስልክን ጨምሮ ማንኛውንም አይነት የዲጂታል ኮሙኒኬሽን ይዘው አይገቡም። በእጅ ሰዓት፣ በጆሮ ጌጥ፣ በጸጉር

የፈተና ሥርዓቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ሽመልስ አብዲሳ

## በሆረ-ፊንፊኔና በሆረ-ሀርሰዴ የተከበረው የኢሬቻ በዓል በሰላም ተጠናቋል

- በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ላደረጉ አካላት ምስጋና ቀርቧል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- መስከረም 21 በሆረ-ፊንፊኔ እንዲሁም መስከረም 22 በሆረ-ሀርሰዴ የተከበረው የኢሬቻ በዓል በሰላም መጠናቀቁን የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ አስታወቁ። በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ የበዓሉን በሰላም መጠናቀቅ አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ በዓሉ በሰላም እንዳይካሄድ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ተቀናጅተው ሴራዎችን ሲሸርቡ ሰንብተዋል። ያም ሆኖ ግን በመላ ኢትዮጵያውያን እና በፀጥታ አካላት ትብብር በዓሉ ያለምንም ችግር በሰላም በመጠናቀቁ የጠላቶቻችን ህልም መክኗል።

በሆረ-ፊንፊኔና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# በ2015 የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት ታቅዶ እየተሰራ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት የንቅናቄ መድረኮች የሚካሄዱ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ሰሞኑን "አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም" በሚል መሪ ቃል 35ኛው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ቀን በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተከበረበት ወቅት እንደ ተናገሩት፤ የቱሪዝም ዘርፉን ለማጠናከር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት ባለድርሻ አካላት መካከል የሰመረ ትብብር በመፍጠር፤ አገልግሎቶችን በማሻሻል፤ ባሕላዊ ቅርሶች እና ተፈጥሮአዊ ሀብቶችን በመጠበቅ፣ በመንከባከብ እና በማልማት የሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ ይደረጋል።

ከአሁን ቀደም እምብዛም ትኩረት ያላገኘው የሀገር ውስጥ ቱሪዝም፤ በቀጣይ ዘርፉን በማነቃቃት የቱሪዝም ገቢ እንዲጨምር ይሰራል ብለዋል። ከዚህ አንጻር በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትና አብሮነትን በማጎልበት ዜጎች የቱሪዝም መስህቦች እንዲጎበኙ፣ ያልተዋወቁ መስህቦችም እንዲያውቁና እንዲያስተዋወቁ በትኩረት እንደሚሰራ ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ፣ ነገን በአዲስ ምዕራፍ ለመስራት ሀገራችን ያጋጠማትን ውስጣዊ ችግሮች እና አሉታዊ ተፅእኖዎች መሰረት በማድረግ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ያለበት ደረጃ በመፈተሽ እና እስካሁን የተጓዝንበትን መንገድ በማጤን በቁርጠኝነት እንደሚሰራ ገልጸው፤ ዘርፉን ለማነቃቃትና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ በዓለምም ሆነ በሀገር ደረጃ የተፈጠሩ የቱሪዝም ለውጦችን የዋጁ አዳዲስ ስትራቴጂዎችና አሰራሮች ይቀየሳሉ ብለዋል።

በዚህ ረገድ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበትና የኢትዮጵያ ከፍታ ዘመን አብሳሪ የሆነው እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግንባታው መገባደድ ላይ ያለው የዓባይ ግድብ አንዱና ትልቁ የቱሪስት መስህብ መሆኑን የጠቆሙት አምባሳደሯ፤ ግድቡን ጨምሮ ተፈጥሮአዊ የቱሪስት መስህቦች ጉብኝት በማጠናከር ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማሳደግ ተገቢ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በተለይ ለቱሪስትና ለኢንቨስትመንት ፍሰት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው የዓባይ ግድብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስፋት መስራት እንደሚገባ



ሻንጋ ፏፏቴ (ከአሶሳ 34 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ)

ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ሰፋፊ እና ዓይነተ-ብዙ የቱሪዝም ሀብቶችና የቱሪስት መስህቦች የድንቃ ድንቅ ተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት ናት ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፤ ሆኖም ግን የሀገሪቱ የቱሪዝም ልማት ጠንካራ እና የተቀናጀ ጥረትን የሚጠይቅ ፈታኝ የልማት መስክ እንደሆነም አልሸሸጉም።

ሀገሪቱ ያላት እምቅ የቱሪዝም ሀብቶችን በዓለም-አቀፍ የቱሪዝም ገበያ በማስተዋወቅ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን በማረጋገጥ የአካባቢውን ማህበረሰብ ህይወት መለወጥ ቀዳሚ ሥራ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ ከዚህ አንጻር የቱሪዝም ዘርፉን ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ እና ስነምህዳራዊ ፋይዳዎችን በኃላፊነትና በዘላቂነት በማልማት ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚቻል አመልክተዋል።

ብሔራዊ ፓርኮችን እና ጥብቅ ስፍራዎች የብዝሀ ሕይወት አካላት ተፈጥሮአዊ ባህሪያቸውን ጠብቀው የሚገኙ ጸጋዎቻችንን በመረዳትና በማልማት፣ ተወዳዳሪ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መፍጠር ላይ በትኩረት መስራት ተገቢ መሆኑንም ጠቁመዋል።

መንግሥትም ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ለቱሪስት መዳረሻዎች መሰረተ ልማቶችን በስፋት እየዘረጋ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሯ፤ ዘርፉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል ተስፋ ከጣለባቸው ቀዳሚ ሴክተሮች አንዱ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በመልማት ላይ የሚገኙ የመዳረሻ ልማትና የቱሪስት መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችም መንግሥት ለዘርፉ ቁርጠኝነት እንዳለው የሚያመለክቱ ናቸው ብለዋል።

ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪና የገቢ መጠን ለመጨመር ለጎብኚዎች በተቻለ መጠን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ይደረጋል ያሉት አምባሳደሯ፤ በተመሳሳይ መልኩ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችና ባለሙያዎች የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ታሳቢ በማድረግ ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት እንደሚሰራም አብራርተዋል።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አሻድሊ ሀሰን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሀገሪቱ ብሔራዊ ኩራት ምንጭና የአዲሱ ትውልድ አዲስ አርበኝነት ተጋድሎ ማሳያ የሆነው የዓባይ ግድብ ከነበሩበት ውስብስብ ችግሮች ተላቅቆ የ3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት ተጠናቅቋል።

በተጨማሪም ክልሉ ክረምት ከበጋ በሚፈሱ ትላልቅ ወንዞች የታደለ፤ እንደ ወርቅ፣ እምነበረድ፣ ድንጋይ ከሰል እና መሰል የማዕድን ሀብቶች የሞሉበት ከመሆኑም ባለፈ ከዓባይ ግድብ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ የቱሪዝም ሀብቶች የክልሉ ከፍተኛ በረከቶች መሆናቸውን ጠቁመው፤ እነዚህ ሀብቶችም ለቱሪዝም እድገት ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው ተናግረዋል።

# የኢሬቻ በዓል በሰላም መጠናቀቁን የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባና በቢሾፍቱ ከተማ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የታደሙበት የሆረ-ፊንፊኔና የሆረ-ሀርሰዴ ኢሬቻ በዓል ያለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም መጠናቀቁን የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል አስታወቀ።

የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይሉ ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ ቅደመ ዝግጅት በማድረግ በቴክኖሎጂ የታገዘ ቅድመ መከላከል ስራን ከህዝቡ፣ ከኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረትና ከበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራቱ በሁለቱም ከተሞች የተከበረው በዓል ሰላማዊ ሆኖ መጠናቀቁን ገልጿል።

በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገው ህዝብ፣ ለኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረትና ለበዓሉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እንዲሁም የተሰጣቸውን ግዳጅ በሚገባ ለተወጡት የፀጥታና ደህንነት ኃይሎች ግብረ-ኃይሉ ላቅ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል።

የሀገራችን ጠላቶችና እነርሱ የሚመሯቸው አሸባሪዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በደህንነታችን ላይ አደጋ ለማድረስ ስለሚጥሩ ህብረተሰቡ አካባቢውን ነቅቶ በመጠበቅ ቀጣይ በሀገራችን የሚከበሩ ሌሎች ህዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ላይም እያሳየ ያለውን ቀና ትብብር አጠናክሮ እንዲቀጥል የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይሉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

# በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ዋለ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በመሬት ሀብት አጠቃቀም ላይ የሚታየውን የአገልግሎት አሰጣጥ፣ የመረጃ አያያዝ ችግር የሚቀርፍ የቴክኖሎጂ መተግበሪያን አበልጽጎ ጥቅም ላይ ማዋሉን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስታወቀ።

የቴክኖሎጂ መተግበሪያው በከተማ አስተዳደሩ በመሬትና መሬት ነክ በሆኑ ጉዳዮችና አገልግሎቶች ዙሪያ የሚንጸባረቁ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሰፊው ሊፈታ እንደሚችልም ተገልጿል።

ክፍለ ከተማው በቴክኖሎጂው ማበልጸግ ስራና በመሬት ሀብት አጠባበቅ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ባለሀብቶች፣ ባለሙያዎች፣ የወረዳ ጽህፈት ቤቶችና ባለድርሻ አካላት እውቅና በሰጠበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቀነአ ያዴታ እንደገለጹት፤ መሬት ውድ፣ ውስን እና ቁልፍ ሀብት ከመሆኑም ባሻገር ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ቢሆንም የመሬት አስተዳደር ስርዓታችን ላይ ያሉ አሰራሮችና አገልግሎት አሰጣጥ በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው።

ዘርፉ ዜጎች ያልረኩበት፣ የስነ-ምግባር ችግር በስፋት የሚስተዋልበትና የሚታማበት በመሆኑ ክፍተቶቹን በመቅረፍ ፍትሀዊነትን ለማስፈን በቴክኖሎጂ መታገዝ ያስፈልጋል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ መሬት አስተዳደር በርካታ አገልግሎትን የሚያቀላጥፉ የቴክኖሎጂ ማልማት ስራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል። ሆኖም ቴክኖሎጂ ብቻውን መፍትሔ ስላልሆነ ከላይ እስከ ታች ያለውን የሰው ሀይል ማብቃት ያስፈልጋል ብለዋል።



ለቴክኖሎጂው እውቅና ተሰጥቷል፤

የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ብሩክ ከድር በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በክፍለ ከተማው በመሬትና መሬት ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የቴክኖሎጂው ሚና ከፍተኛ ነው።

መተግበሪያው በውስጥ አቅም በልጽጎ እጅግ ውስን ሀብት የሆነውን መሬት በአግባቡ በጥቅም ላይ ለማዋል መሰራቱ ወሳኝ እርምጃ መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በክፍለ ከተማ ውስጥ ያለው የመሬት አስተዳደር ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ስነ-ምግባር፣ ሙያዊ እገዛና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎትን የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በክፍለ ከተማው ውስጥ ያለውን መሬት የምንመለከትበት አይን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ነው ያሉት ዶክተር ብሩክ፣ የምንሰጠው አገልግሎት ከእጅ መንሻ ነፃ በሆነና ለዚያም በሚያግዝ አግባብ በቴክኖሎጂ ታግዘን ህዝብን ማገልገል አለብን ሲሉም ተናግረዋል።

የክፍለ ከተማው የመሬት ልማት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ሕይወት ተፈራ በበኩላቸው፤ ጽህፈት ቤቱ በውስጥ አቅም በራሱ ባለሙያዎች የቴክኖሎጂ መተግበሪያውን ማበልጸጉን ጠቅሰው፤ መተግበሪያው መሬትና መሬት ነክ ጉዳዮችና አገልግሎቶች ላይ ተግባራዊ መደረጉን አመልክተዋል።

ኤል ኤም አይ ኤስ (LMIS) በሚል የሚታወቀው መተግበሪያው ኢንፎዴስክና የቴሌግራም ቦታ እንዳለው ጠቁመው፤ የመሬት ይዞታ መረጃ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጡ በመተግበሪው ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ይደረጋል ብለዋል።

የቴክኖሎጂው አበልጻጊ አቶ እዮኤል አለማየሁ በበኩላቸው፤ የቴክኖሎጂ መተግበሪያው ተገልጋዮች ባሉበት ስፍራ ሆነው ጥያቄያቸውን ማቅረብ፣ ጥያቄያቸው ምን ላይ እንደደረሰና ፋይሉም ከየትኛው ሰራተኛ እንዲሁም አመራር ጋር እንዳለ በቀላሉ ማወቅ ያስችላቸዋል ሲሉ ስለ ቴክኖሎጂው አብራርተዋል።

እንደ አቶ እዮኤል ማብራሪያ፣ ቴክኖሎጂው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በክፍለ ከተማው የተለያዩ ሁኔታዎችን ተጠቀመው በኃላፊዎች፣ በግለሰቦችና ባለሙያዎች መካከል የሚፈጠሩ ጣልቃ ገብነቶችንም ያስቀራል።

ቴክኖሎጂው በየቀኑ የሚመጡ የተገልጋዮችን ብዛት ከማሳየቱም በተጨማሪ ከመጡት ተገልጋዮች ምን ያህሉ ተገቢውን አግልግሎት እንዳገኙና እንደተስተናገዱም የተብራራ ሪፖርት ይሰጣል ያሉት ባለሙያው፤ በክፍለ ከተማው ዙሪያ በተጠኑ ካርታዎች ላይ የነበሩበትን የተበታተነና በባለሙያዎች እጅ የነበረውን አሰራር በማስቀረት የመረጃ ቅብብሎሽን ቀልጣፋና በቀላሉ ተደራሽ ያደርጋልም ብለዋል።

የቴክኖሎጂው መተግበሪያ በፈጻሚዎች በኩል ሊከሰት የሚችለውን አድሎዓዊ አሰራር በመግታት ወቅታዊ የሆኑ ሪፖርቶችን ከማግኘት አኳያ 80 በመቶ ችግሮችን እንደሚቀርፍ የጠቁሙት አቶ እዮኤል፤ ለደንበኞች ንብረትም አስፈላጊውን ጥቅል መረጃ እንዲይዝ ተደርጎ መሰራቱን አብራርተዋል።

ዜና

# ጠንካራ ዲፕሎማሲና ህግ የማስከበር ስራ የሽብርተኞችን እንቅስቃሴ መግታት አስችሏል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ጠንካራ የዲፕሎማሲና የሉዓላዊነት ማስከበር ዘመቻ ላይ በትኩረት በመስራቷ የሽብርተኞች እንቅስቃሴ በአጭሩ ሊገታ መቻሉ ተጠቆመ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአረብኛ ቋንቋ መምህር እና ጋዜጠኛ አቶ ኡመር መኮንን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሱ ጫናዎች በየወቅቱ እየጨመሩ እንደመሄዳቸው መጠን በዚህ ልክ በተሰራው የዲፕሎማሲ፣ የሚዲያና ሉአላዊነት የማስከበር ዘመቻ እየተገታ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ለነጮች ቅኝ አለመገዛቷና ለመላው ጥቁር አፍሪካውያን የነፃነት ምሳሌ መሆኗ በበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የምትታወቅ መሆኗን አውስተው፤ ነጮች በተለይም አንዳንድ ምዕራባውያን ይህን ቂም ለመወጣትና ሀገሪቱን በእነሱ ቁጥጥር ስር ለማዋል በኢትዮጵያ ላይ ጫናዎችን ሲያደርጉ እንደሚስተዋል ጠቁመዋል።

በተለይም ከዓባይ ግድብ ጋር ተያይዞ፣ የአፍሪካውያን ችግር በአፍሪካውያን ብቻ መፈታት አለባቸው የሚሉ አቋሞቿ በአንዳንድ የውጭ ኃይሎች ዘንድ የሚወደዱ ባለመሆናቸው የተለያዩ የሽብር ቡድኖችን በማስማራትና በመደገፍ በርካታ ጫናዎች እንደሚደረጉባት ተናግረዋል። በተለያየ መልኩ የሚደረጉ ጫናዎችን ለመመከትና ሀገሪቱ እራስዋን ለመከላከል የምታደርገው እንቅስቃሴ ጠንካራ መሆኑንም ገልፀዋል።

ትህነግ ለሶስት አስርተ አመታት ገደማ ሀገሪቱን በሚመራበት ወቅት ሀገሪቱን ከተለያዩ ጥቃቶች ለመጠበቅ ተብሎ በህዝብ ሀብት የተገዙ በርካታ የጦር መሳሪያዎች ቡድኑ በሚገኝበት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ብቻ ተገድበው በተቀመጡበት ወቅት እንኳ ኢትዮጵያን ማንበርከክ አለመቻላቸው ትልቅ ማሳያ ሊሆን እንደሚችልም አስታውቀዋል።



አቶ ኡመር መኮንን

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገራዊ ተልዕኮ ያለው ጠንካራ መከላከያ ኃይል በመገንባቷ ሀገሪቱ እራስዋን ለመከላከልና ሉአላዊነቷን ላለማስደፈር የምታደርገው ጥረት እጅግ አኩሪ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ኡመር ገለፃ በዓባይ ግድብ ምክንያት በሀገሪቱ ላይ በርካታ ጫናዎች ሲደርሱ ቆይቷል። የኢትዮጵያ ጠላት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በመምጣት አልሸባብና አልቃይዳን በመደገፍና በማሰማራት ኢትዮጵያን ለማሸበር ሞክረዋል።

ይህንን የውጭ ጠላቶች ድርጊት ለመቀልበስ ኢትዮጵያ ከሀገራቱ ጋር መልካም የሚባል ግንኙነት በመፍጠር በኩል በተሰራው የዲፕሎማሲ ስራ ስኬትን ለማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

አፍሪካውያን ጉዳዮቻቸውንና ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ በምታራምደው ጠንካራ አቋምም በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ከኢትዮጵያ ጎን እንዲቆሙና ሀገሪቱ በቀጣናው ያላት ተሰሚነት እያደገ መምጣቱን የሚያመላክት መሆኑንም ተናግረዋል።

ምዕራባውያን ሽብርተኝነትን እንደሚዋጉና እንደሚያወግዙ በተለያየ መልኩ ሲገልፁ ቢሰማም ጥቅማቸውን በሚያስጠብቅ መልኩ ሊደግፉ እንደሚችሉ አቶ ኡመር ጠቅሰው፤ ከጥቅማቸው ጋር ብቻ በማስተሳሰርም ጭምር የሚደግፉበት አግባብ እንዳለ ጠቁመዋል።

በሚዲያ በዲፕሎማሲ እንዲሁም በውስጥ ደግሞ ጠንካራ የመከላከያ ሰራዊት ግንባታ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ተጠብቆ እንዲቀጥል የሚያደርግ መሆኑን አመላክተዋል።

ቀጣይም በሀገሪቱ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ጫናዎችና ትንኮሳዎች የማይጠፉ መሆኑን በመገንዘብ የውስጥ አንድነትን በማስቀጠል በዲፕሎማሲው በኩል የተጀመሩ መልካም ስራዎች በማስቀጠል፣ በሚዲያ ዘርፉም የሀገሪቱን እውነታ በማሳየት እንዲሁም የውስጥ አንድነቶችን የሚሸረሽሩ ተግባራት ላይ መዝመት ይጠበቃል ብለዋል። በተጨማሪም በተቻለ መጠን በሽብርተኛ ኃይሎች ላይ የሚወሰደው ወታደራዊ እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ጠቁመዋል።

# በክልሉ ከ301 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል

## - 7 ነጥብ 7 ሚሊየን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በመኸር እርሻው 301 ሺህ 556 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በዘንድሮ ግብርናም ከክልሉ 7 ነጥብ 7 ሚሊየን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ክንፉ የመኸር ምርት እና ቀጣይ የበጋ መስኖ ስንዴ የተሰራበትን ሁኔታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስረድተዋል።

በክልሉ በመኸር ዋና ዋና ሰብሎች በስንዴ፣ ባቄላ፣ አተር፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ጤፍ የመሳሰሉትን ሰብል በዘር ለመሸፈን በማቀድ አጠቃላይ 311 ሺህ 394 ሄክታር መሬት የታረሰ ሲሆን እስካሁንም 301 ሺህ 556 ሄክታር በዘር የተሸፈነ መሆኑን ገልጸዋል።

በመኸሩ ወቅቱ የተስተካከለ የዝናብ ሁኔታ ቢኖርም የግብዓት አቅርቦት እና ምርጥ ዘር በሰብል ሽፋኑ ላይ ማነቆ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ በስንዴ ከፍተኛ የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት እንደነበረም ገልጸዋል። በመጀመሪያዎቹ የስንዴ የዘር ወራቶች ላይ 22 ሺህ 51 ሄክታር ለመሸፈን ታቅዶም 24 ሺህ ሄክታር ያህል መሬት የታረሰና የለሰለሰ መሆኑን አስታውሰዋል።

በክልሉ የዘር ፍላጎቱን ቀድሞ ማሳወቅ ቢቻልም ይሄንንም ለመሸፈን የሚያስችል የዘር አቅርቦት በክልሉ ውስጥ የዘር ማበጠሪያና አቅራቢ ድርጅቶች ያልነበሩ በመሆኑና ምርጥ ዘር ከርቀት ተጓጉዞ የሚመጣ መሆኑ ዘር በወቅቱ ማድረስ እንዳልተቻለም ተናግረዋል።

በወቅቱ ወደ ክልሉ የገባው ኤምፒኤስ(ዳፕ) ወይም ቅይጥ ማዳበሪያ የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶአደሮች እንዲሰራጭ መደረጉን ያስታወሱት አቶ አሸናፊ፤ ዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ ግን ዘግይቶ በመግባቱ የተፈጥሮ ማዳበሪያን(ባዮ ፈርትላዘርን) በአማራጭነት ለመጠቀም መቻሉንም ገልጸዋል።

በቀጣይ በክልሉ የተዘሩ ሰብሎችን የአረም ቁጥጥር፣ የሰብል በሽታ እና የተባይ ዳሰሳና ክትትል ስራዎችም የሚሰሩ መሆኑን አመላክተዋል።

በክልሉ በ2014 የምርት ዘመን 431 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ መስኖ በዘር መሸፈኑንም አቶ አሸናፊ ተናግረዋል። ለዚህም በክልሉ በሚገኙ ስድስት ዞኖች ያለውን የውሃ መሰረተ ልማቶችን፣ ባህላዊ መስኖዎችንና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም እስከ 18 ሺህ ሄክታር በዘር ለመሸፈን ታቅዷል ብለዋል።

ከፌደራል መንግሥት የተለያየ ድጋፍ እየቀረበ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ፤ 62 የውሃ ፓምፖች እየተዘጋጁ ናቸው ብለዋል። ይህ ሲቀርብም እንደ ክልሉ የውሃ መሰረተ ልማት እይታ እና የመስኖ ውሃ መሰረተ ልማት እይታ ባህላዊ የመስኖ ውሃ እይታን ታሳቢ ያደረገ የበጋ ስንዴ ዘር ሽፋን ይኖራል። ለዚህም የዳሰሳ ጥናት በስፋት እየተሰራ ነው፤ የማሳ ልኬት፣ የቴክኒክ ኮሚቴ እና የዐብይ ኮሚቴ ምስረታ ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተጠናቀቁ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በክልሉ በሜካናይዜሽን ምርት ለማምረት በመኸር በተሰሩ ስራዎች 40 ያህል ትራክተሮች ተገዝተው ገብተዋል። ከፋ ዞን 25 ትራክተሮች ገብተዋል ያሉት ሌሎች ዞኖችም ተጨማሪ ትራክተሮች ገዝተው ያቀረቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ የደረሱ ሰብሎችን ከብክነት ለመከላከል የተሻሻለ የምርት ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ከመጠቀም አኳያ በኮምባይነር እና ሌሎች የምርት መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ምርት የመሰብሰብ ልምዱ በኢንቨስተሮችም ጭምር ዝቅተኛ መሆኑን አመላክዋል።

ነገር ግን እስካሁን ድረስ ከኢንቨስተሮች በኪራይ በመግዛት በከፋ ዞን በጊምቢ ወረዳ በኮምባይነር የማጨድ እና ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራ ተጀምሯል ብለዋል። ይሄንን ለማስፋፋት እና በቀጣይ በሁሉም አካባቢዎች ለመጠቀም የቅድመ ዝግጅት እና ድጋፍ ከሚሰጡ እና ከሚያከራዩ ድርጅቶች ጋር ውይይቶች ተጀምረዋል ብለዋል። በቀጣይ መሰረተ ልማት ባለባቸው እና ኩታ ገጠም እርሻዎች አካባቢ ኮምባይነሮች በስፋት ይገባሉ ብለዋል።

ክልሉ ሰፊ የእርሻ መሬት እና የውሃ ሀብት ያለው ቢሆንም የመሰረተ ልማት ችግር አንጻር በሙሉ አቅሙ ለማምረት ገና በጅምር ላይ ቢሆንም ሙሉ አቅሙን በማቀናጀት ሀገሪቱ ከውጭ የምታስገባውን የስንዴ ምርት ማስቀረት የሚቻልበት፣ የምግብ አቅማችን የምናረጋግጥባትና የገጽታ ግንባታችንን ከፍ የምናደርግበት ስለሆነ በዞን፣ በወረዳ እና እስከ ቀበሌ ያለው የግብርና ቢሮ መዋቅር በተጠናከረ ሁኔታ በመደጋገፍ ስኬታማ የበጋ መስኖ ስንዴ ማምረት እንደሚገባ አመላክተዋል።

በተጨማሪም ተዘርተው በማሳ የሚገኙ ሰብሎች በተለያየ የሰብል ጥበቃ ስራዎች እና እንክብካቤ ጉድለት የምርት መቀነስ እንዳይከሰት በየደረጃው ያለው ሁሉም አካል የራሱን ኃላፊነት እንዲወጣም መልዕክት አስተላልፈዋል።

በኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ከሚታረሰው መሬት 25 በመቶው በኩታ ገጠም ታርሶ በዘር መሸፈን አለበት በሚል ከዞኖች ጋር በመግባባት ወደ ስራ መውረዱን አስታውሰው፤ እስካሁን ባለው የአጠቃቀም ግምገማ ከ70 በመቶ በላይ በኩታ ገጠም ታርሶ በዘር ተሸፍኗል። ይህም በክልሉ በጅምር ደረጃ ጥሩ የሚባል የኩታገጠም የአስተራረስ ዘይቤ እየተተገበረ ያለበት መሆኑንም አመላክተዋል።

ለኩታገጠም አንዱ መነሻ የተሟላ የግብዓት አቅርቦት ወቅቱን የጠበቀ የእርሻ ሥራ እና ወጥ የሆነ የእንክብካቤ እና የምርት አሰባሰብ የተሰባሰበውን ምርት ለገበያ የማቅረብ ሥርዓቱ አንድ ላይ የሚመራ ነው ያሉት ይህንን ከማድረግ አኳያ አንዳንድ አካባቢዎች ክፍተቶች ይታያሉ። በበልግ የተዘሩ ሰብሎች ውጤታማ የሚባል የኩታ ገጠም አሰራር ተከትለዋል። መኸርም ላይ ስንዴ እና በቆሎም በሚዘራባቸው አካባቢ ላይ አመርቂ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህን አጠናክሮ መቀጠል የሚገባ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህ በእንዲ እንዳለ የክልሉ ግብርና ቢሮ ለሀገር መከላከያ ሰራዊት ድጋፍ ከማድረግ አንፃር ከዚህ በፊት ሙሉ ሰራተኛውና አመራሩ የአንድ ወር ደመወዙን የደገፈ መሆኑን ገልጸው፤ በሶስተኛው ዙር ጦርነቱም ወደ ግንባር በመሄድም፣ የተሽከርካሪ እና የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ለማስገባት በእንቅስቃሴ ላይ ነው ብለዋል።

በኩንታል ደረጃ የሚለኩ የተለያዩ ሰብሎችን ለመከላከያ ድጋፍ እና ወደ ግንባር ለሚገቡ ልዩ ኃይሎች ድጋፍ እያደረገ ነው ያሉት ክልሉ አዲስ ክልል እንደመሆኑ የተሽከርካሪ እጥረት ቢኖርበትም አንድ ተሽከርካሪ ሁለት አመራር እንዲጠቀም በማኔጅመንቱ ተወስኖ አንድ የመስክ መኪና ለልዩ ኃይሉ እና ወደ ግንባር ለሚሄዱት የአምቡላንስ አገልግሎት እንዲሰጥ ድጋፍ መደረጉንም ጠቁመዋል።



አቶ ወንዳጥር መኮንን

# በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ የውሃ መሰረተ ልማቶች ተጠግነው ለአገልግሎት በቁ

## - በወረራው በውሃ ተቋማት ላይ የ1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ውድመት ደርሷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ በ512 ሚሊዮን ብር ወጪ በአሸባሪው ትህነግ ወረራ በውሃ ተቋማት ላይ በደረሰው ውድመት ለችግር ተዳርገው የነበሩ ዜጎች ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኙ ማድረጉን አስታወቀ፡፡ በወረራው በውሃ ተቋማት ላይ ብቻ የአንድ ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ውድመት መድረሱ ተገልጿል፡፡

በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወንዳጥር መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ትህነግ ከምስረታው ጀምሮ የአማራን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጆ የተነሳ በወረራ ወደ አማራ ክልል ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በመጀመሪያ የሚያጠቃው ሕዝባዊ ተቋማትን ነው፡፡

በውሃ ተቋማት ላይ የደረሰው ጉዳት በወረራ ውስጥ የነበሩትን ብቻ ሳይሆን በወረራ ከተያዙ አካባቢዎች የሚመጣ ውሃን ይጠቀሙ የነበሩ የሌሎች አካባቢ ዜጎችንም በእጅጉ የፈተነ ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ርብርብ የወረራውን መቀልበስ ተከትሎ ቢሮው ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በ512 ሚሊዮን ብር የአስቸኳይ ጊዜ ሥራ በመሥራት ዜጎች በአፋጣኝ ውሃ የሚያገኙበትን መንገድ ለመፍጠር በተደረገው ጥረት ዜጎች ለዕለታዊ ፍጆታ የሚሆን ውሃ እንዲያገኙ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ውሃን ለዜጎች ለማድረስ በተደረገው ጥረት ውስጥ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ አካላት መሳተፋቸውን የጠቆሙት አቶ ወንዳጥር፤ በዚህም ችግሩን ለመቅረፍ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

አሸባሪው ትህነግ በርካታ የመጠጥ ውሃ ተቋማት፣ የሕክምና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ሌሎችም ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመትና ዝርፊያ መፈጸሙን ጠቅሰው፤ በውሃ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ ማሽኖችን፣ ተሽከርካሪዎችንና ጀኔሬተሮችን በመዝረፍ፣ ግዙፍ የውሃ ታንከሮችን በማፍረስና ቢሮዎችን ጨምሮ የውሃ ተቋማትን ሙሉ በሙሉ በማውደም በውሃ ተቋማት ላይ ብቻ የአንድ ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ውድመት አድርሷል ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ህግ በጦርነት ወቅት ማኅበራዊ ተቋማትን ማውደም የተከለከለ መሆኑን አቶ ወንዳጥር ጠቁመው፤ የሽብር ቡድኑ ግን ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ የህዝብ መገልገያዎችን ማውደም የመጀመሪያ ስራው አድርጎት እንደነበር ተናግረዋል፡፡

በወቅቱ የትህነግ አባላት መሰረተ ልማቱን ካወደሙ በኋላ፤ ሕዝቡ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት በእግሩ ተጉዞ ያመጣው የነበረውን ውሃም ቤት ለቤት ዞረው በመቀማት ለወታደሮች ሲያከፋፍሉ እንደነበርም አቶ ወንዳጥር ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ተቋማቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ መሠረተ ልማቶችን በዘላቂነት መልሶ ለመገንባትና ለመጠገን ከፍተኛ ሀብት እንደሚጠይቅ ያስታወሱት አቶ ወንዳጥር፤ ተቋማቱን መልሶ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ባለሀብቶች፣ ረጂ ድርጅቶችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ኢሬቻ ትውፊቱን ሳይለቅ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ የበዓሉ ተሳታፊዎች አሳሰቡ

## - የኢሬቻ በዓል በሆረ-ሀርሰዴ ተከብሯል

**ፍቃዱ ዴረሳ**

ቢሾፍቱ፡- ከቀደምት አባቶቻችን የወረስናቸውን ሰላማዊ የኢሬቻ እና ሌሎች ባህሎቻችን ትውፊታቸውን ሳይለቁ ለቀጣዩ ትውልድ ሊተላለፉ ይገባል ሲሉ የኢሬቻ በአል ተሳታፊዎች አሳሰቡ። የሆረ-ሀርሰዴ ኢሬቻ በዓል በትናትናው እለት በቢሾፍቱ ከተማ ተከብሯል።

በበዓሉ ላይ አባ ገዳ ጎበና ሆላ፣ አባ መልካ ሆረ-ቢሾፍቱና ሌሎች አባገዳዎች እንዲሁም ሃደ ሲንቄዎች የኢሬቻ በዓሉን በኢሬፈና ስነ ስርዓት አከናውነዋል።

በምረቃቸውና ምስጋናቸውም ዝናቡን የሰላም አድርጎ ያሳለፈው ፈጣሪ አዝመራውን የሰላም፣ ዘመኑንም የጥጋብ እንዲያደርግ ተማፅነዋል።

በርካታ የበአሉ ተካፋዮችና እንግዶች ከተለያዩ አካባቢዎች በመጡ አባገዳዎች እና ሀደ-ሲንቄዎች እየተመሩ ወደ ሆረ-ሀርሰዴ በማምራት የኢሬፈና መርሃ ግብር አከናውነዋል።

የምስጋናና የምልጃቸው ዋና ጭብጥም ፈጣሪ ዘመኑን እንዲባርክ፣ አዝመራውም እንዲያፈራ፣ በሀገሪቱም ሰላም እንዲወርድ ተማፅኗቸውን ለፈጣሪ ማቅረብ ነው።

የሆረ-ሀርሰዴ ኢሬቻ በዓልን ለማክበር በቢሾፍቱ ከተማ የተገኙት ታዳሚዎችም በባህላዊ አልባሳት በማጌጥ በጭፈራና ህብረ ዝማሬዎች በመታጀብ ወደ ሆረ-በመጓዝ የኢሬፈና መርሃ ግብር አከናውነዋል።

ኢፕድ ካነጋገራቸው ተሳታፊዎች መካከል የአዳማ ከተማ ነዋሪ አባ ገዳ በዳዳ ጂማ ከጥንት አባቶቻችን የወረስነውን ሰላማዊ የኢሬቻ ባህሎቻችን እሴቶቻቸውን ሳይለቁ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል ብለዋል።

የዚህ ዓመት ኢሬቻን ልዩ የሚያደርገውም ክብረ በዓሉ በፍፁም ሰላማዊና በእርስ በእርስ መዋደድ የተከበረ መሆኑን ተናግረው፤ በቀጣይም ባህሎቻችን ላይ ጠባሳ ከሚጥሉ ተግባራት በመራቅ ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪ የሆነው ወጣት ምትኩ ደስታ በበኩሉ በየአመቱ በድምቀት የሚከበረው የሆረ-ሀርሰዴ ኢሬቻ በአል በቢሾፍቱ የሚከበር በመሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የኦሮሞ ብሔር ባህላዊ አልባሳት፣ ጭፈራ እንዲሁም ሌሎች ባህሎችን የማወቅ እድል እንደሰጠው ገልጿል። በዚህም ወጣቶች ባህሎቻችንን በማወቅ በተገቢው ማንፀባረቅና ለሌሎች ባዕድና መጤ ባህሎች ሰለባ እንዳይሆን ወጣቱ ትውልድ እራሱን መምሠል ይጠበቅበታል ብሏል።

በሌላ በኩል ከአርሲ አካባቢ የመጣችው የበዓሉ ታዳሚ ወይዘሪት ፋዮ ተማም ቄሮዎች የአባ ገዳዎችን ምክርና ፈለግ በመከተል እኛ ቀሬዎች ደግሞ የሀደ ሲንቄዎችን ፈለግ በመከተል የኢሬቻን በአል ጨምሮ ሌሎች እሴቶቻችንን በመቀበል ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል ብላለች።

የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሀደ ሲንቄ ሹካሬ ቦረና በበኩላቸው፤ የቢሾፍቱ ከተማ በዓሉን ለማክበር የሚመጡ ተሳታፊዎችን በሰላም ተቀብላ የምትሸኝ ከተማ መሆኗን ተናግረዋል።

የኦሮሞ ህዝብ የራሱ የገዳ ነጸብራቅ የሆነ የኢሬቻ በዓል እንዳለው ገልጸው፤ ወጣቶች የታላላቆቻቸውን ምክርና መልካም እሴት በመተግበር ሀገር አሁን ካለችበት ሁኔታ ውስጥ ሊያወጡ ይገባል ብለዋል።

የኢሬቻ በዓል በአዲስ አበባ በሆረ-ፊንፊኔና በቢሾፍቱ ሆረ-ሀርሰዴ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በተገኙበት ሰላማዊ በሆነና በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ አልፏል።

# በሆረ-ፊንፊኔና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ ሽመልስ እንዳሉት፤ ከውጭ ሆነው ገንዘብ በመመደብ በዓሉን ለማወክ ሲሰሩ የነበሩ ጠላቶች ነበሩ፤ ነገር ግን የነዚህ ጠላቶቻችን ሴራ አልተሳካም፤ በዓሉም በሰላም ተጠናቋል።

በሁለቱም ቀናት በተከናወነው በዓል ከአስር ሚሊየን በላይ ህዝብ የተሳተፈበት ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ በዓሉ የኢትዮጵያ ትልቅነት የታየበት ሆኖ ተፈጽሟል፤ የኦሮሞ ህዝብም ትልቅነቱን ያሳየበት ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ህዝብም ሆነ የቢሾፍቱ ህዝብ በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን የጠቀሱት አቶ ሽመልስ፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብም በዓሉ በሰላም እንዲካሄድ ላበረከተው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ በራሴና በኦሮሚያ ክልል ስም ምስጋና አቀርባለሁ ብለዋል።

የአዲስ አበባ እና የቢሾፍቱ ህዝብ በየቦታው ምግብና መጠጥ እንዲሁም ማረፊያዎችን በማዘጋጀት የበዓሉ ታዳሚ ያለድካም በዓሉን በደስታ እንዲያከናውን ላበረከተው ድጋፍም ምስጋና አቅርበዋል።

የፀጥታ ኃይሎችም ይህ በዓል ያምንም ችግር እንዲከናወንና የጠላቶች ሴራ እንዲመክን ቀንና ሌሊት ላደረጉት አስተዋፅኦ ምስጋና አቅርበዋል።

የበዓሉ ተሳታፊዎችም የኦሮሞንም ሆነ የመላውን ኢትዮጵያ መልካም እሴት በኢሬቻ በማሳየታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ያሉት አቶ ሽመልስ፤ የምንከበርበት እና ከፍ የምንልበትን ባህል በማሳየታችሁ ልትከበሩ ይገባል ብለዋል። በዓሉን በፍቅር፤ በሰላም፣ በአንድነት በማክበራችሁ እናመሰግናለን ሲሉም ምስጋና አቅርበዋል።

ባህል ለሀገር እድገት ጠቃሚ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሽመልስ፤ ከሁሉ በላይ ሀገራችን ከፍ የምትለው ባህልን ስናከብር ነው፤ ስለዚህ የኦሮሚያ ባህል እንዲያድግ በየደረጃው ያለው አመራር ላደረገው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

የሚዲያ ተቋማት ስለበዓሉ ፋይዳ በመግለጽና የበዓሉን እሴቶች በማስተዋወቅ ረገድ ለተጫወቱት አይተኬ ሚናም ርዕሰ መስተዳድሩ አመስግነዋል።

ትናንት ተደብቀን ስናከብር የነበረው የኢሬቻ በዓል ዛሬ ግን በሚሊየኖች የሚሳተፉበት፤ ኦሮሞም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያከብረው መሆን ችሏል፤ ይህን ለማሳደግ ሁላችንም ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

# «ኃያላን ሀገራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ገለጹ። የኢትዮ-ኩባ የህዝብ ለህዝብ ወንድማማችነት መድረክ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ የኩባ አምባሳደር ሆርጌ ለፌብሬ ኒኮላስ፤ ኃያላን ሀገራት ኢትዮጵያን ምን እና መቼ ማድረግ እንዳለባት ሊነግሯት አይችሉም፤ ተቀባይነትም አይኖረውም። የሀገሪቱን ሉዓላዊ፣ የህዝቡን ተፈጥሯዊ እና ነፃ ውሳኔ ማክበር ግዴታቸው ነው ብለዋል።

ኩባውያን ሁልጊዜም ከኢትዮጵያ ጎን ቆመን ለሀገሪቱ ሉአላዊነት እንሟገታለን፤ ኢትዮጵያ ሉአላዊነቷን ለማስከበር ማንኛውንም ውሳኔ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የመወሰን መብቷ ምሉዕ መሆኑን አንዳንድ ሀገራት የዘነጉት ይመስላል ሲሉም ነው የተናገሩት።

የተባበሩት መንግስታት የሚመለከታቸው አካላትም ኃላፊነታቸውን ከአድሎ በፀዳ መልኩ በአግባቡ ሊፈፅሙ ይገባል። አንዳንድ ኃያላን አገራት ይህንን በመጠቀም የራሳቸውን ፍላጎት ለመጫን መሞከራቸውን ሊያቆሙ ይገባልም ሲሉም አሳስበዋል። ኢትዮጵያ ያጋጠሟትን ፈተናዎች ለማለፍ በምታደርገው ጥረት ሁሉ የኩባ ድጋፍ እንደማይለይም ነው የገለጹት።

በሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ዶክተር አለሙ ስሜ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያ ከወዳጆቿ ጋር ያሳለፈቻቸውን ጥሩ ጊዜ ለማመስገን፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን ወዳጅነት በማጠናከር ከአፍሪካና ከአለም ሀገራት ጋር በጋራ ለመበልጸግ ለሚደረግ ስራ የሚያግዝ ነው።

ሀገር ተረካቢ ወጣቶች ወዳጅ ሀገራት ጋር በመሄድ በጋራ ችግኝ መትከል፣ የወዳጅነት ማዕድ መቁረስና በአዲስ አበባ የሚካሄድ የወደፊት ወጣት አመራሮች የሚሳተፉበት ጉባኤ መታሰቡን አንስተው፤ መርሃ ግብሩ የዚህ አካል እንደሆነም ተናግረዋል። የአፍሪካ ወጣቶች ሕብረት በኢትዮጵያ ለማቋቋም የተያዘውን እቅድ እንደሚያግዝም አመልክተዋል።

ሀገራቱ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው፣ በተመሳሳይ ትግል ያለፉና በአለም አቀፍ መድረኮችና በሁለትዮሽ ትብብር በመደጋገፍ ግንኙነቱን ለማጠናከር በማለም የተዘጋጀ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይፋ ከተደረጉ መርሃ ግብሮች መካከል ወጣቶችን ማዕከል ያደረጉ የሃሳብ ፕሮጀክቶች በድርጊት ትግበራቸውን የምናሳይባቸው አካል ነው ብለዋል።

በኩባ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዶክተር ገነት ተሾመ እንደገለጹትም፤ የወንድማማችነት ምሽቱ ሁለቱ ሀገራት ምን ያህል ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ያመላክታል። ኩባውያን ወታደሮች በኢትዮጵያ የከፈሉት መስዋዕትነት ክብር ይገባቸዋል። ሀገራቱ ይህን በሚመጥን መልኩ በተለያዩ ዘርፎች ጠንካራ ትስስር ፈጥረዋል። በጤና፣ ግንባታ፣ ቴክኖሎጂ፣ በትምህርት፣ በንግድ እና በሌሎችም ዘርፎች አመርቂ ትብብር እያደረጉ ይገኛሉ።

የሕወሓትን አጠቃላይ እንቅስቃሴና ለሰላም ፍላጎትና ዝግጁ አለመሆኑን የአለም አቀፍ ማሕበረሰብ እንዲገነዘብና ጫና እንዲፈጥር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል። አለም አቀፍ ማሕበረሰብ የቡድኑን ሁኔታ እየተገነዘቡትም ለቡድኑ ያደላ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ ብለዋል።

ኩባዎች በተለይ በሰብአዊ መብት ካውንስል ውስጥ አባል በመሆናቸው የኢትዮጵያን ትክክለኛ አቋም በማንጸባረቅ፣ በድምጻቸው በመደገፍ እና ሌሎች ካሪቢያን ሀገራትን በማስተባበር ድጋፍ ያደርጋሉ ሲሉም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያም ኩባውያንን ትደግፋለች። በተመሳሳይ ሁኔታ የምዕራቡ አለም ጫና ያለባቸው ናቸው። ከ60 ዓመታት በላይ ማዕቀብ የተጣለባት ሀገር ናት። ይህንን ማዕቀብም ኢትዮጵያ በመቃወም ከኩባ ጎን በመሰለፍ ትስስርና ድጋፍ የሚደረግበት አግባብ አለ ብለዋል።

ኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ከዚያድባሬ ስርዓት ጋር በተደረገው ውጊያ በርካታ ኩባውያን ተሳታፊ እንደነበሩ ይታወሳል።

# የፈተና ሥርዓቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጌጥና በመሳሰሉት መንገዶች እንዳያልፉ በፍተሻ ተረጋግጠው እንዲገቡ በማድረግ ተማሪዎች ከተጭበረበሩ መልሶች እንዲድኑ የሚደረግበት ስርዓት ዘርግተናል። ተማሪዎች በከፍተኛ የፍተሻ ስርዓት እንዲያልፉ ይደረጋል ብለዋል።

አሰራሩ በእውቀታቸውና በልፋታቸው ልክ ተማምነው እንዲሰሩ እንደሚያደርግ፣ ለትምህርት ስርዓቱ መሻሻል አንድ እመርታ መሆኑንም ተናግረዋል። ‹‹ውሳኔው ከተወሰነ ጊዜ ጀምሮ በጎበኘናቸው አብዛኞቹ ክልሎች የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ተፈታኞችን በክረምት ወቅት ሲያዘጋጇቸው ተመልክተናል›› ሲሉም ተናግረዋል።

ጸረ ሕዝብ አቋም አንግበው ድርጊቱን የሚያራምዱም ሆነ፣ የተወሰኑ አካባቢዎችን ለመጥቀም በማሰብ የሚፈጸመውን ስርቆት፣ ሌብነትና ማጭበርበርን ለመከላከል ስርዓቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውም ጠቁመዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዓላማው የትምህርት ጥራት በተማሪዎች፣ በመምህራን እና በትምህርት ቤቶች ጥረት እንዲረጋገጥ ማስቻል እንጂ፤ የአላፊና ወዳቂ ተማሪዎችን ቁጥር መጨመርና መቀነስ አለመሆኑንም ነው ዶክተር ፋንታ የገለጹት።

አንድን አካባቢ ለመጥቀም ታስቦ የፈተናውን ስርዓት ለመናድ የሚደረገውን እና ፈተናው ወጥቷል በሚል በማህበራዊ ሚዲያ በማሰራጨት ተማሪዎች ውጤታቸው እንዲበላሽ ሲደረግ የነበረውን አሰራር እንደሚያሻሽለውም እምነታቸውን ገልጸዋል።

በተለያዩ አካባቢዎችም የመንግስትን ኃላፊዎችና ስራ ላይ የተሰማሩትን ጨምሮ አመኔታ የጎደለበት ክስተት በመስተዋሉ ወላጆች፣ ተማሪዎች እና መምህራን በውጤቱ ላይ አመኔታ እንዲያጡ በማድረግ መሰረታዊ ችግር የሆነውን አሰራር ለማረም እንደሚያግዝም አመልክተዋል።

ውሳኔው ተማሪዎች 12 ዓመታት የደከሙበትን የብሄራዊ ፈተና ተረጋግተው እንዲሰሩ፣ ለሀገር ጠቃሚ፣ ለራሳቸውም እድገትን የሚያረጋግጡ ተማሪዎችን በውጤታቸው መዝኖ ለማሳለፍ የሚያስችል እንደሆነ ዶክተር ፋንታ ተናግረዋል።

ይህ የተደረገውም አንድን አካባቢ ለመጥቀም ተብሎ ከሚሰራው በተጨማሪ በስርዓተ ትምህርቱ እና በፈተና ሂደት አመኔታ እንዲታጣበት ለማድረግ ሆን ተብሎ ሲሰራ የነበረ ሴራ መሆኑንም ነው የገለጹት።

በዩኒቨርሲቲ እንዲሰጥ ያስገደደውም የፈተናዎቹን መውጣት ተከትሎ በዚህ ስርዓት ተማሪዎች ፈተና እንዲደርሳቸው ብቻ ሳይሆን የተሳሳተ መልስ እንዲደርሳቸው በማድረግ ከፍተኛ ስራ መሰራቱንም ነው ያስታወሱት።

ፈተናውን በኦን ላይን ለማድረግ መንግስት ሰፊ ስራ ሲሰራ መቆየቱን ያስታወሱት ዶክተር ፋንታ፤ ተማሪዎቹን አንድ ለአንድ ለማድረስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ስርጭት ከፍተኛ ሀብት መጠየቁን አመልክተዋል።

እነዚህን ማሟላትና ሌሎች አገራት የደረሱበት ዘመናዊ አሰራር ላይ እስኪደረስ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ላይ ተማሪዎችን አምጥቶ በመፈተን፣ ፈታኞቻቸውን ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን በማሳተፍ ፈተናቸውን ጨርሰው ወደ መጡበት አካባቢ እንዲመለሱ ማድረግ ጠቃሚ ነው ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመስከረም በዓላት የኢትዮጵያን ታላቅነት፤ የሕዝቡን አንድነትና ሰላም ወዳድነት አረጋግጠዋል!

ኢትዮጵያ በውስጥም በውጪም ጠላቶቿ ተናብበውና ተቀናጅተው ሁሉን አቀፍ ጦርነት በከፈቱባት በዚህ ወቅት፤ ወርሃ መስከረም አቅፎ የያዛቸውን በርከት ያሉ የአደባባይ በዓላትን በሰላም አክብራ ታጠናቅቃለች፤ ኢትዮጵያውያንም በዚህ መልኩ በአንድ ላይ ቆመው የጋራቸው የሆኑ በዓላቶቻቸውን በአደባባይ ደምቀው ማክበር ይችላሉ ብሎ ልቡን ሞልቶ የሚናገር ካለ ምናልባት እሱ የኢትዮጵያን ትልቅነት፣ የኢትዮጵያውያንም የሰብዕና ከፍታ የተገነዘበ ሀገርና ሕዝብ ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በግንባር ጦር መዝዘው ከሚዋጓት ጀምሮ፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ብሎም ዲፕሎማሲያዊና የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ላይ በተመሰረተው ውንጀላ በጠላቶቿ የተከፈተባት ጦርነት እግር ከወርች ወጥሮ በያዛት በዚህ ወቅት፤ በመስከረም ወር ያሉ በርካታ እና ብዙ ህዝብም አደባባይ ወጥቶ የሚያከብራቸውን በዓላት በሰላም እንዳይከናወኑ በጠላቶቿ የተወጠኑ የሽብርና ኹከት ሴራዎች በመኖራቸው ነው።

ይሄን እውነት የተመለከተ ታዲያ ኢትዮጵያ በዚህ ልክ በአደባባይ የሚከበሩ በዓላቶቿን በሰላም አክብራ ታልፋለች፤ ኢትዮጵያውያንም ለማክበር ዓደባባይ የሚወጡለት በዓልን እንዳሰቡት በሰላም አክብረው ወደቤታቸው ይመለሳሉ ብሎ በሙላት ባያስብ የሚፈረድበት አይሆንም። ምክንያቱም በአንድ በኩል ዘርፈ ብዙ ጦርነት ተከፍቶ ያንን የመመከት ከፍ ያለ የቤት ስራ በመኖሩ የጸጥታ ኃይሉ ለአደባባይ በዓላት በሰላም መከበር የሚተርፍ አቅም የለውም የሚል የጠላት የተዛባ ምስል ቀረጻ በመኖሩ ነው። በሌላ በኩል በእነዚሁ ጠላቶች በሕዝቦች መካከል የመከፋፈልና የመጠላላት ስሜትን ለመፍጠር ከበዓላቱ ቀድሞም ሆነ በዓላቱ እየተከበሩ ባሉበት ሂደት ውስጥም ከፍ ያለ አንዱን በአንዱ ላይ ለማነሳሳት የሚያስችላቸውን ሴራ ሲፈጽሙ በመቆየታቸው ነበር።

በዚህ ረገድ በተለይ የመስቀል በዓልን እና የኢሬቻን በዓል ከሁሉም በላቀ መልኩ የሁከትና ብጥብጥ አውድ ለማድረግ እነዚህ የሀገር እና የሕዝብ ጠላቶች ከፍ ያለ እቅድና ዝግጅት ነበራቸው። ለዚህ ደግሞ አንዴ እምነትን፣ ሌላ ጊዜ ብሔርን የታከኩ የማደናገሪያና ማስመሰያ የጥፋት ተግባራትን እዚህም እዚያም ሲለኳኩሱ መቆየታቸው ማሳያ ነው። በተለይ በአማራ እና ኦሮሞ ሕዝቦች መካከል አንዱ የአንዱ ጠላትና አጥፊ አድርጎ ለመሳል የተሞከረበት ሂደት ከመስቀል በዓልም በላይ ኢሬቻን የኹከትና ሽብር ማዕከል አድርጎ ለመጠቀም የወጠነ ከፍ ያለ እቅድ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ የእኩያን ሴራ እና ዝግጅት አንድም በጸጥታ ኃይሉ ከፍ ያለ ዝግጅትና ሥራ፤ ሁለተኛም፣ በሕዝቡ አንድነትና ሰላም ወዳድነት ሳይሳካ ቀርቷል።

ይልቁንም እነዚህ ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በሁሉም አካባቢዎች የነበሩ ወርሃ መስከረም በጉያው አቅፎ የያዛቸው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በዓላት፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ በአንድነት፣ በወንድማማችነትና ሁሉም የእኔ ነው በሚል ስሜት በጋራ አደባባይ ወጥተውና ደምቀው ያሳለፏቸው ሆነዋል። ለምሳሌ፣ ያሆዴ፣ ዮ..መስቃላ፣ ጊፋታና ሌሎችም በዓላት፣ ቀደም ሲል በጠላት ሴራ በህዝቦች መካከል ተፈጥሮ የነበረን መጠራጠርና ቂም የሻሩ፤ በወንድማማችነት ሕዝቦች በፍቅርና በይቅርታ አንድ ላይ ቆመው የጠላትን ሴራ መስበር የቻሉባቸው ሆነው አልፈዋል። ሲዳማው ከወላይታው፣ ወላይታው ከጋሞው፣ ጋሞው ከሃዲያው፤... ሁሉም እንደ ባህልና ወጉ አንዱ የአንዱ ድምቀትና አለኝታ ሆነው የተገለጡበት ነበር።

በመስቀል በዓል በተለይ ደግሞ በደመራው ምሽት ላይ የታየውም ይሄው እውነት ሲሆን፤ የመስቀል በዓል የአንድ ሃይማኖት ወይም ህዝብ ሳይሆን፤ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ቅርስ፤ ከፍ ሲልም የዓለም ሀብት መሆኑን ከምንጊዜውም በላይ ወዳጅም ጠላትም እንዲገነዘበው አድርገው በጋራ አክብረውት አልፈዋል። የኢሬቻ በዓልም እንዲሁ በሆራ ፊንፊኔም ሆነ በሆራ ሀርሰዴ ኢትዮጵያውያን ከየአቅጣጫው ተሰባስበው በአንድ ሆነው በልዩት መካከል ያለን ውበት፤ በሕብረት ውስጥ ያለን ጥንካሬና አሸናፊነት ያስመሰከሩበት ሆኗል። በእነዚህን በዓላት የበለጠ በአብሮነት ደምቀው የመዋልና የማክበራቸው ተግባር ደግሞ፤ ኢትዮጵያውያን ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ ከአንዱ ጋር ሆኖ ስለሌላኛው ባህልና እሴት እውቀት እንዲቀስሙ የሚያስችላቸው እና ኢትዮጵያን የበለጠ የሚያገዝፉት ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያንም የበለጠ ሕብረትና አንድነታቸው በመተዋወቅ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያደርጉ እንጂ የሚያጎድሉ አለመሆናቸውን በግልጽ የተናገረ ነው።

እነዚህ የበዙ የመስከረም ወር በዓላት ታዲያ፤ ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷን ሳያስደፍር ከዘመን ዘመን አስከብሮ የሚያኖራት ጀግና ሕዝብ ባለቤት ከመሆኗ ባሻገር፤ ምን ያህል የገዘፈና ታላቅነቷን የሚያሳይ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ተፈጥሯዊ እምቅ አቅም እንዳላት ያስመሰከሩ ሆነው አልፈዋል። ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ፣ ለጠላት ወሬና ሴራ ቦታ የማይሰጡ፤ ጊዜያዊ ፈተናና ችግሮች የማይፈትኗቸው፤ ይልቁንም ጠላት ሲበዛባቸው የበለጠ የሚሰባሰቡ፤ ሴራ ሲከፋባቸው የበለጠ አንድ ሆነው የጠላትን የሴራ ቋጠሮ ውል አልባ የሚያደርጉ፤ ስለ አንድነትና ሰላማቸው ድርድር የማያውቁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ይህን በማድረጋቸውም ለኢትዮጵያውያን በክብራቸው ልክ፤ ለጸጥታ ኃይሉም በተግባሩ መጠን ምስጋና ይገባቸዋል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ኢሬቻ ከምስጋና ባሻገር...

ሰላማዊት ውቤ

የኢሬቻ በዓል ከጥንት ጀምሮ የኦሮሞ ሕዝብ ሲያከብረው የኖረ የምስጋና በዓል ነው ። አባ ገዳ ጎበና ሆላ የቱለማ አባ ገዳና የኦሮሞ አባ ገዳዎች ሕብረት ፀሐፊና የኢሬቻ በዓል ሰብሳቢ እንደሚናገሩት ኢሬቻ የሚለው ቃል በራሱ ምስጋና፤ መስማማት፣ አንድነት፣ እርቅ ፣ማለት ነው። የገዳ ሥርዓት ባለበትና የኦሮሞ ሕዝብ በሚገኝበት ሁሉ ይከበራል።

በኢሬቻ በዓል ውስጥ የሚደረጉ የተለያዩ ሥርዓቶችም አሉ። የአኮሌ ሥርዓት አንዱ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የወለዱ ከብቶች ይመረቁበታል። ጊደሮች ወተታቸው ተጠራቅሞ፣ ግማሹ ተንጦ፣ ቅቤው ወጥቶ፣ ግማሹ እርጎ፣ ግማሹ አይብ ተደርጎ ቅንጬ ተሰርቶ፣ ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ ከተመረቁ በኋላ ይበላል።

ኢሬቻ ብዙ አይነት ቢሆንም ዋናዎቹ ሁለት ናቸው። ኢሬቻ መልካ (Irecha Melka) እና ኢሬቻ ቱሉ (Irecha Tullu ) ፤ኢሬቻ መልካ ፤በውሃ ዳርቻ ክረምት እንደወጣ ይከበራል። ይበልጡን ምድርን በዝናብ ያጠገበውን አምላክን በምስጋና የመዘከር በዓል ነው። ኢሬቻ ቱሉ ፤በተራራ ጫፍ ላይ በበጋው መሀል ይከበራል። ዝናብን በወቅቱ የሚሰጠውን አምላክ በበጋውም ወራት ለእንስሳቱ መልካሙን ዝናብ እንዲሰጥ እንስሳት እንዳይሞቱ ይለመናል። ይበልጡን የፀሎት በዓል ነው። ቢሆንም...ቡራኬው፤ ምስጋናው፤ ፀሎቱ በሁለቱም ኢሬቻ አይቀርም።

አንዳንድ ሰዎች ከፈጠራ ወሬም ሆነ ከሀሜት ተነስተው እንደሚሉት በአድ አምልኮ ማራመጃና ከክፉ መንፈስ ጋር የሚገናኝ አይደለም። በዓሉ ሲከበር ለተራራው ወይም ለወንዙ አይሰገድም። እነሱን ለፈጠረ ፤ አምላክ ነው የሚሰገደው። በኦሮሞ ባህል ልምላሜ እና ውሃ የአምላክ መንፈስ ማደርያ፤ ንፁህ የአምልኮት ስፍራ ነው ተብሎ ይወሰዳል። ለፀሎት ምቹ እና ሰላማዊ ቦታ ነው የሚል የፀና ዕምነት አለ። እናም በኢሬቻ መልካ በዓል የተፈጥሮን ኡደት ሳያዛባ ያስቀጠለ አምላክ ይመሰገናል። አምላክ ይከበራል፣ አምላክ ይመለካል።

በዓሉ የሚከበረው ታላቁ የወራት አውራ መስከረም ወር ላይ ነው ። በመሆኑም ኢሬቻ በክረምት ወራት ዘመዳማሞች በዝናብ እና በውሃ መሙላት ምክንያት ተራርቀው ሳይገናኙ ክረምቱን ስለሚያሳልፉ ውሃው ሲጎድል እግዚአብሄር ታረቀን፣ ምህረት አደረገልን፣ በውሃው መሙላት ምክንያት የተለያየን ቤተሰቦች እግዚአብሔር እንድንገናኝ አደረገን ብሎ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት ከገዳ ሥርዓት አንዱ ነው ማለት ይቻላል። ክረምቱ ካለፈ በኋላ የወንዙ ሙላት ከጎደለ እሩቅ ያሉ ዘመዳማሞች ይገናኛሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ የኢሬቻ በዓል ዘመን የሚለወጥበት ቀን ጭምር ነው። ኦሮሞ በእድሜያችን ላይ አዲሱን ዘመን ጨመርክልን ብሎ አምላኩን ያመሰግንበታል።

ኢሬቻ በዓል ዋቄፈና ከተባለውና ከጥንቱ የኦሮሞ ሕዝብ እምነት የፈለቀና ገና ሲወለዱና በዳዴ ከሚሄዱበት ጀምሮ ቋንቋ መናገር ሲጀምሩ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የሰጠው ፀጋ ነው ይላሉም አባ ገዳ ጎበና ሆላ። ዋቄፈና የሐይማኖቱ ስም የእምነቱ ተከታይ ዋቄፈታ ተብለው እንደመጠራታቸው እንዲሁም ፈጣሪ አምላክ የሚመሰገንበት በመሆኑ ሐይማኖታዊ በዓልም ነው ኢሬቻ።

"ኢሬቻ ማለት ዋቃ (ፈጣሪ) ማለት ነው የሚሉት የኦሮሞ ታሪክ ምሁሩ ዲሪቢ ደምሴም ይሄን ከክረምት መውጫና ከበጋ መግቢያ ጋር ተያይዞ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረብን የተመለከተ የአባ ገዳውን ሃሳብ የሚጋራ ሃሳብ ያንፀባርቃሉ። ኢሬቻ የፈጠረውን ማመስገን ማለት ነውም ይላሉ። የአንትሮፖሎጂ ባለሙያዎችም ይሄንኑ ሃሳብ ይጋራሉ። ሁሉም ኢሬቻ ማኅበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ልዩነት ሳይደረግ በፈጣሪው የሚያምን ሁሉ በአንድነት ወጥቶ ለዘመናት በጋራ ሲያከብረው የኖረ የኦሮሞ ሕዝብ የአደባባይ በዓል ነው። የገዳ ሥርዓት አካልም ነው።

ታሪክ ፀሐፊዎቹና የታሪክ ድርሳናት እንደሚናገሩትም ኢሬቻ የኦሮሞ የገዳ ሥርዓት መገለጫም ተደርጎ ይወሰዳል። የኢሬቻ በዓል ከ6 ሺ 660 ዓመት በፊት መከበር መጀመሩንም ያነሳሉ። ከዚህ ጊዜ አንስቶ በዓመት ሁለት ጊዜም ሲከበር ቆይቷል። የመጀመሪያው ክረምት መውጣትን ተከትሎ በውሃማ አካባቢዎች የሚከበርበት ነው። ሁለተኛው ደግሞ በበልግ ወቅት ግንቦትና ሰኔ ወራት ውስጥ በተራራማ አካባቢዎች ይከበራል። ይሄ አሁን አሁን እየተረሳ መጥቷል።

በዓሉ በአዲስ አበባ መከበር ከጀመረም ዘንድሮ አራተኛ ዓመቱን ይዟል። አዲስ አበባ ከተማ ላይ በዓሉን የማክበሩ ሂደት በ2012 ዓ.ም እንደ አዲስ አለመጀመሩና በተለያዩ ሁኔታዎች ተቋርጦ የቆየ መሆኑ ይወሳል። አንዱ ምክንያት የምስጋና በዓሉን ከበዓድ እምነት ጋር የሚያያይዝ የሰዎች አመለካከት ነበር ይላሉ። ለምሣሌ ቡና አንዳንድ ሰዎች በዘልማድ ቡና ማፍላት፣ ዛፍ ቅቤ መቀባት፣ ስለት ማግባት፣ ሽቶ ውሃ ውስጥ መወርወር ሲደረግበት ስለምናይ በዓድ አምልኮ ነው ይላሉ ። ነገር ግን ይሄ አይፈቀድም።

በዚህ የተነሳም በዓሉ እውነተኛ ታሪክና ቱፊቱን በሳተ ትርጓሜ ምክንያት መከበር እንዳቆመ ይነገራል። በዓሉ በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዲ ኃይቅ መከበር ከጀመረ በኋላም የጥፋት ኃይሎች አይን ማረፊያ በመሆን የግጭትና ሁከት ማእከል ለማድረግ ብዙ ተሞክሯል። ሩቅ ሳንሄድ በ2008 ወይም የዛሬ ሰባት ዓመት አካባቢ በዓሉ ሲከበር በነበረበት ወቅት የተፈጠረው ሁከት ጥሩ ማሳያ ነው። ሁከቱ መንግሥትን በተቃወሙ ወጣቶችና በመንግሥት ኃይሎች መካከል ግጭት በመፈጠሩ ወይም ልዩ የፖለቲካ ፍላጎት በነበራቸው የጥፋት ኃይሎች መሆኑ አያጠራጥርም።

የጥፋት ኃይሎቹ በሁከቱ በተኩስ፣ በአስለቃሽ ጭስ፣ በመረጋገጥ እና ገደል ውስጥ በመግባት በርካታ ፈጣሪያቸውን ለማመስገን የወጡ የበዓሉ ታዳሚዎች ሕይወት እንዲያልፍ አድርገዋል። የውጭና የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ዘግበውት እንደነበረው በሁከቱ ምክንያት የበዓሉ አከባበር ሥነስርዓት ተስተጓጉሏል።

የምስጋና በዓሉ ከዚህ በኋላ በነበሩት ዓመታት በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዲ ኃይቅ ሲከበር እንዲሁም ባለፉት ሦስት ዓመታት በአዲስ አበባ ሲከበር የጥፋት ሃይሎች ያቀዱት አለመደገሙ ያስደስታል። ምክንያቱ ደግሞ አንደኛው በዓሉ በከተማዋ አስተዳደር ብርቱ ጥንቃቄ ተደርጎ በመከበሩ ነው።

ሁለተኛው ሕዝቡ ለፈጠራ ወሬዎችና ለአሉባልታ ወይም ልዩ የፖለቲካ ፍላጎት ላላቸው ክፍሎች ጆሮውን ባለመስጠቱ ነው። ሦስተኛው ምክንያት በዓሉን መላው ሕዝብ በዓሌ ነው ብሎ በመቀበሉ ነው። ለዚህ በአዲስ አበባ ባሉ ሁሉም ክፍለ ከተሞች ሕብረተሰቡ በነቂስ አደባባይ ወጥቶ ያከበረው መሆኑ በምሳሌነት ይነሳል። የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት መስህብ እንዲሁም የክልሉና የሀገሪቱ የማይዳሰስ ቅርስ ገቢ ከመሆኑ አንፃርም ፋይዳው ቀላል አልነበረም።

ለአብነት የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ እንደሚናገሩት በ2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተከበረው ኢሬቻ ሆራ ፊንፊኔ ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ቱሪስት ተካፍለዋል። ይህ ለቱሪዝም ገቢ መጎልበት ከፍተኛ ፋይዳ አለው።

ከኢሬቻ ጋር ተያይዞ በቢሾፍቱ የተከበረው ሲደመርበት ገቢው ምን ያህል ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በአሁኑ ወቅት የኢሬቻ በዓል መከበር እየተጠናከረ ከኢትዮጵያ ባሻገር በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር አባላት በዓሉን በድምቀት ያከብሩታል።

በሆራ አርሰዲ ሐይቅ በየዓመቱ በዓሉ ሲከበር በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ይታደማሉ። ለምሳሌ በ2010 ዓ.ም ከተማዋን የጎበኙ የአገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ቁጥር ከ2006 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር ከ260 ሺህ ወደ 343 ሺህ 861 አድጓል። ገቢው በቁጥር ቢጠቀስ በገቢ ደረጃም ከአራት እጥፍ በላይ ብልጫ አለው። ዘንድሮ መስከረም 21 ቀን 2015 በሚከበርበት በሀገራችን ዋና መዲና እንዲሁም ነገ መስከረም 22 ቀን 2015 በሚከበርበት ቢሾፍቱ ምን ያህል የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች እንደሚታደሙበት፤ ከነዚህም ምን ያህል ገቢ እንደሚገኝ አስቦ ማክበር ያለው ፋይዳ ቀላል አይሆንም። መልካም በዓል!

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ፋሽን በወንዶች ጸጉር ቁርጥ

**ተገኝ ብሩ**

የወንዶች ጸጉር እንክብካቤና ቁርጥ ቀድሞ በቤተመንግስትና በከፍተኛ ባለስልጣናት እንደተጀመረ ይነገራል፡፡ ነገስታትና የነገስታት ልጆች ጸጉራቸውን በተለየ መልኩ አሳምረውና አበጅተው ህዝብ ፊት ይቀርቡ እንደነበርም የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ይህ የጸጉር ቁርጥ ልምድም ቀስ በቀስ ከቤተ መንግስት በመውጣት ወደ ማህበረሰብ ወርዶ በርካቶች ዘንድ ደርሷል፡፡

በተለይ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃና 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በተለያየ አይነትና ምርጫ በተለይ ወንዶች ረገድ በስፊው ታይቷል፡፡ ወንዶች ጸጉራቸውን ተስተካክለውና አስተካክለው ውበትን ተላብሰው መታየት ጀምረዋል፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ላይ ወታደሮች ይቆረጡት የነበረው የጸጉር ቁርጥም ለብዙ ዓመታት የበርካታ ወንዶች ምርጫ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ዛሬ ላይ ፋሽን መልከ ብዙ ሆኗል፡፡ የወንዶችን የጸጉር ቁርጥ ዘመኑ ባፈራቸው መሳሪያዎች ታግዞ ማስዋብ ቀላል ሆኗል፡፡ ወንዶችም ጸጉር መድመቂያና ውበት መሆኑን ተገንዝበዋል፡፡ ለጸጉር አቆራረጣቸውም ልዩ ትኩረት መስጠት ጀምረዋል፡፡

በርካቶችም ከዘመንና ወቅት ጋር፣ለበዓላትና ለአዘቦት ቀን ለተለያየ ጊዜና ቦታም ሁኔታው የሚፈቅደውና እንዳሉበት ስፍራ የተለመደ መልክና ቀለም ያለው የጸጉር አቆራረጥ ‹‹ስታይል” ምርጫቸው ሲያደርጉ እያስተዋልን እንገኛለን፡፡

,ኢትዮጵያዊያን ለዘመናት በራሳቸው የጸጉር አሰራር ፋሽን ሲከተሉ ኖረዋል፡፡ ጥንት ወጣቶች ጸጉራቸውን አጎፍረው አንዳንዴም ሹሩባ ተሰርተው ይታዩ ነበር፡፡ የህፃናትና ታዳጊዎች ቁንጮ እንዲሁም የነገስታቱ ሹሩቧም ለዚህ ማሳያዎች ናቸው፡፡




ዛሬ ላይ በየመንደሩ በዘመናዊ መልክ እየተለመዱ የመጡ የጸጉር አሰራር ፋሽኖች፤ ትላንት ኢትዮጵያዊያን በራሳቸው ይዋቡባቸው ከነበሩት የጸጉር አሰራሮች ጋር እጅጉን የተቀራረበ መሆኑን ማየት ይችላል፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ዛሬም ድረስ ሳይቋረጡ ያሉት የጸጉር ማስዋብና እንክብካቤዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ለዘመናት የአፋር ወንዶች ጸጉራቸው በተለያየ ዕፅዋት በመንከባከብ በመጠቅለልና ወዛማና አንፀባራቂ እንዲሆን የማድረግ ጥበብ ዛሬም ድረስ ከተሜዎች መጠነኛ ለውጥ በማድረግ በፋሽንነት ይተገብሩታል፡፡

አሁን ላይ ለጸጉራቸው ልዩ ትኩረት የሰጡት ወንዶች ጸጉራቸውን ዘመኑ ባፈራቸው የተለያዩ ማሽኖችና የጸጉር ቁርጥ መስሪያ ቁሳቁሶች በመታገዝ በውበት ባለሙያዎች ወይም የጸጉር አስተካካዮች ይዋባሉ፡፡ ወንዶቹ ከሌሎች ተመልክተው አልያም ጸጉር ቤት ገብተው የሚፈልጉትን የጸጉር አስተካካይ ለባለሙያዎቹ በመንገር ይዋባሉ፡፡

ሰይድ አከመል ይባላል፡፡ደንበኞቹን በፈለጉት እና ወቅቱ ባመጣቸው መሳሪያዎች በመጠቀም ላለፉት 4 ዓመታት በጸጉር አስተካካይነት ሙያ እየሰራ ይገኛል። በሙያው በቆየባቸው ዓመታትም በየወቅቱ የተለያየ ፋሽን ያላቸው የጸጉር ቁርጦች ቢኖሩም በአብዛኛው በወንዶች ዘንድ የሚመረጠው የፀጉር ቁርጥ ግን ተመሳሳይ መሆኑን ይናገራል፡፡

የጸጉር ቁርጥ አይነቶቹ በእድሜ እና በሰዎቹ ፍላጎት የሚወሰን መሆኑን የሚናገረው ሰይድ፤ በተለይ ህጻናቱ በራሳቸው ምርጫ የሚስተካከሉት አልፎ አልፎ ቢሆንም በአብዛኛው ግን በወላጆቻቸው ምርጫ ላይ ተመስርተው መሆኑንም ይገልፃል፡፡ ብዙዎች በተለይ በእድሜ ገፋ ያሉት አንድ ቁጥር ወይም ኖርማል የተሰኘው ቁርጥ እንደሚመርጡ ይናገራል፡፡

እንደ ሰይድ ገለፃ፣ በበርካታ ወጣቶች ዘንድ እንደ ፋሽንነት የሚወሰደውና የሚወደደው ‹‹ፍሪዝ›› የሚባለው አይነት ነው፡፡ ከስር ዙሪያውን ምልጥ ተደርጎ ወይም በጣም በአጭሩ ተቆርጦ ከፍ እያለ ሲሄድ ጥቁረቱ እየጨመረ ሙሉ በሙሉ በመተውና ቀንሶ በማስተካከል ብቻ በተለያዩ ቅባቶች ጸጉሩን መጠቅለል (መፈረዝ) ነው፡፡

ሰይድ፣ከፍሪዝ ባሻገር አዲስና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የተመለከቱትን የጸጉር ቁርጥ አይነት ምርጫቻቸው የሆነ ደንበኞችም አሉት፡፡ከተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችና ድረ ገጾች በተመለከቱት የጸጉር ቁርጥ መስተካከልም እየተለመደ መቷል፡፡ በተለይ ቅርፆችና ምስሎች በጸጉራቸው ላይ በተለየ መልኩ እንዲሳልላቸው ወይም በልዩ ሁኔታ እንዲሰራላቸው የሚፈልጉም በርካታ መሆናቸው ናቸው፡፡

በተለያዩ ፀጉር ማስተካከያ ቤቶች ውስጥም በፎቶግራፍ በተደገደ መልኩ የጸጉር ቁርጦች ስታየል በ‹‹ሜኖ›› መልክ ይሰቀላል፡፡ሰይድ እንደሚያስረዳው፣ የጸጉር ቁርጦቹ አይነትና እና ስያሜ ከቦታ ቦታ እንዲሁም ከቤት ቤት ይለያያል፡፡

ከዋና ዋናዎቹ የጸጉር ቁርጥ አይነቶች መካከልም ፓንክ (በወጣቶች የሚመረጥ)፣ የላኛው የጸጉር ክፍል ሳይነካ ከስር ብቻ ማስተካከልና ቅርጹን ማስተካከል(ፍሪዝ)፣ዜሮ በአንድ ቁጥርና በሁለት ቁጥር(የማስተካከያ ማሽን ጥርሶች ናቸው) መካከለኛ አጭር ቁርጥ፣ አፍሮ(ቀደም ሲል በብዛት የነበረና አሁንም አልፎ አልፎ ያለ)፣ ጆንትራ ቮልታ፣ ባላቶሊ የተለመዱና ጎልተው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

‹‹የወንዶች ጸጉር ቁርጥ በዘመናት ሂደት ውስጥ እየተለዋወጠ አንዴ ፋሽን ሆኖ ቆይቶ እየጠፋ መልሶ ከመጠነኛ ለውጥ ጋር የሚመጣ ነው የሚለው››ባለሙያው፣አንድ የጸጉር ቁርጥ አይነት ለበርካታ አመታት ፋሽን ሆኖ ሊቆይ እንደሚችልና የሴቶቹን ያህል በዘመን ሂደት ውስጥ የጎላ ለውጥ ሲኖረው እንደማይታይም ይጠቅሳል፡፡

ሰይድ እንደሚያስረዳው፣ወንዶች የሚቆረጡት የጸጉር ቁርጥ እንደ እድሜያቸው ምርጫቸውም የተለያየ ነው፡፡በየጊዜው የሚለመዱ የጸጉር ቆረጣ ስልቶች ወይም ፋሽኖች በአብዛኛው በወጣቱ ዘንድ ይዘወተራሉ፡፡ እድሜያቸው ከፍ ያሉትና በአነስተኛ የእድሜ ደረጃ የሚገኙ ወንዶች በአንፃሩ የተለመደና ብዙም ወጣ ያላለ አቆራረጥን ምርጫቸው ያደርጋሉ፡፡

የጸጉር አቆራረጥ ስልቶች በእድሜ እንደሚለያይ ሁሉ ወቅት ወይም ክረምትና በጋን መሰረት አድርጎም ሊመረጥ ወይም ሊወሰን ይችላል፡፡ክረምት ላይ አሳጥሮ መቁረጥ ይቀንሳል፡፡ከዚህ ይልቅ ጸጉር ባለበት መንከባከብና ቅርጹን ማስተካከል በብዙዎች ይዘወተራል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በጋ ላይ አሳጥሮ በተለያየ ቅርጽ መሰራትን ብዙዎች ያዘወትራሉ፡፡ይህም የብርድና የሙቀት ወቅት መሆን የሚፈጥረው ምርጫ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ የወንዶች የውበት ሳሎኖች ውስጥ የፀጉር ቁርጥ ዋጋ ከ40 ብር እስከ 300 ብር ይገኛል፡፡ ለዋጋው መለያየትም እንደየ ቤቱ የፀጉር ማስተካከያ መሳሪያዎች ጥራት፣ የውበት ሳሎኖቹ የሚገኙባቸው ቦታና የፀጉር አስተካካዮች ልምድ መሰረት ያደረገ እንደሆነም መረዳት ይቻላል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የለቅሶ ነገር

**አቤል ገ/ኪዳን**

ባህላችን ፈጣን የሆነ ለውጥ እያስተናገደ ነው። ግሎባላይዜሽን(ሉላዊነት) ቀስ በቀስ ተጽእኖውን እያሳረፈብን እንደሆነ በግልጽ እየታየ ነው፡፡ አኳኋናችን በሙሉ ተቀይሯል፡፡ የአለባበስ ባህላችን በጣም ተቀይሯል፡፡ አነጋገራችንም እንደዚያው፤ አመጋገባችንም እንደዚያው ሌላውም ሌላውም...፡፡ በየፈርጁ በጣም ብዙ ለውጦች እየተከሰቱ ነው፡፡ እነዚህ ለውጦች የት እንደሚያደርሱን አይታወቅም፡፡ ምን እንደሚያስከትሉብንም ለመረዳት ከመሀል ነጠል ብሎ ወጥቶ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ለጊዜው ግን ለውጦቹ በጣም ግዙፍ እና ፈጣን ስለሆኑ ቆም ብሎ ማሰቢያ እድል አልተገኘም፡፡

የሆነ ሆኖ የዛሬው ጉዳያችን ስለ ለውጥ ለማውራት ሳይሆን ለውጥ ካጠቃቸው ባህሎቻችችን አንዱ የሆነውን የለቅሶ ባህላችንን ለመቃኘት ነው፡፡ የለቅሶ ባህላችን ሳይታሰብ ዲጂታል እየሆነ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ኦንላይን እየሆነ ነው፡፡ ሲለቀስ ፤ ሲቀበር ፤ የማጽናኛ ስብከት ሲሰጥ ወዘተ...ሁሉም ነገር በቀጥታ ስርጭት በማህበራዊ ሚዲያ የሚታይ ጉዳይ እየሆነ ነው፡፡ አሁን ላይ ብዙ ሰዎች የሚያውቋቸው ወይም የሚወዷቸው ሰዎች መሞታቸውን የሚረዱት በፌስቡክ ነው፡፡ ለቅሶ የሚደረሰውም እዚያው ፌስቡክ ላይ ነው፡፡ እርም የሚወጣውም እንደዚያው፡፡

እርግጥ ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነውና ቴክኖሎጂን መጠቀም ምንም ክፋት የለውም፡፡ ነገር ግን ሀዘን ደግሞ ግላዊ እና አካላዊ ስሜት ነው፡፡ ማልቀስ ፤ መታመም ፤ መጨነቅ ፤ መደንገጥ ፤ የአካል አለመታዘዝ እና መሰል ስሜቶች ይኖሩታል፡፡ ሰዎች በሀዘን ወቅት ደግሞ እነዚህን የስሜት ውጣ ውረዶች እንዲያልፉ እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን ስልክ እና ካሜራ አጠገባቸው ተደቅኖ እንዴት ብለው ይህን ነገር ይወጡት፡፡ የአርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ቀብር ቀን ያየነው ይሄንን ነበር፡፡ ካሜራ ይዘው ከሚራወጡት ብዙ ሰዎች በተጨማሪ ሁሉም ስማርት ስልክ የያዘ ሰው በሙሉ የቀጥታ ስርጭት አስተላላፊ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ቀራጭ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ሰው ሞቶ ቀብር ላይ ያለን ሳይሆን አንድ የሽልማት ፕሮግራም ላይ የታደምን ነበር የሚመስለው፡፡ አንዳንዶቹም እዚያው ሀዘንተኞች አጠገብ ቆመው በቀጥታ ስርጭት እያስተላለፉ ላይክ እና ሰብስክራይብ አድርጉን ሲሉ ሁሉ ይሰማ ነበር፡፡ ያሳፍራል፡፡ ሰዎች ሀዘናቸውን እንዲወጡ የተወሰነ ክፍተት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ፈረንጆቹ በዚህ ብዙ ስለተማረሩ እና ልምድም ስለቀሰሙ ለቅሶ ሲኖርባቸው አንዳንድ የለቅሶውን ጉዳዮች ከየትኛውም አይነት ሚዲያ እይታ የተከለከለ እንደሆነ ያሳውቃሉ። እኛም ጋር እንዲህ አይነት ነገር ሊለመድ ይገባል። አልቅሰህ እንኳ በማይወጣልህ ሀዘን ውስጥ ሆነህ ጭራሽ እንዳታለቅስ እየተከታተሉ የሚያውኩህን ባለ ካሜራዎች አትምጡብኝ ማለት አግባብ ነው፡፡

ሌላኛው በጣም አሳፋሪ ነገር ደግሞ ለቅሶ ላይ ሄዶ ከለቅሶው አላማ ውጭ የግል ጉዳይን መፈጸም ነው፡፡ በግልጽ ለማስቀመጥ ያህል ለቅሶ ላይ ሄደው የሚያደንቁትን ሰው ሲያገኙ ለቅሶውን ትተው አድናቆታቸውን ለመግለጽ እና ፎቶ ለመነሳት አጋጣሚውን የሚጠቀሙበት ሰዎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ጭራሽ የሚያደንቁትን ሰው ለማግኘት ብቻ ብለው ቀብር እንደሚመጡ በሚያስታውቅ ሁኔታ ተደናቂውን ሰው ሲከታተሉ ነው የሚውሉት፡፡ እንዲህ አይነቱ ነውረኝነት ሟችንም መናቅ ተደናቂውንም ሰው ሀዘኑን እንዳይገልጽ ማወክ ነው፡፡ ይሄ ዘመን ያመጣው አሳፋሪ ባህል ነው፡፡

ሌላኛው ደግሞ ለቅሶን የግል ትርኢት ለመስራት የሚጠቀሙት ጉደኞች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ የሚያለቅሱት ሁሉ ካሜራውን እየተከተሉ ነው፡፡ ሌሎቹ ካሜራ አይን ውስጥ ለመግባት ለየት ብለው ይቀመጣሉ ፤ ወይም ለየት ያለ አለባበስ ይለብሳሉ ወይም የሆነ ወጣ ያለ ነገር ያደርጋሉ፡፡ የግል የገጽታ ግንባታቸውን ለማካሄድ ለዚያ ቀን ብቻ ልብስ የሚገዙ ወይም መኪና የሚይዙ ወይም ከእነሱ የበለጠ ታዋቂ ሰው ስር ልጥፍ የሚሉም አሉ። ድሮ ሀዘን ሲኬድ ሀዘንን በሚገልጽ እና የሀዘንተኛን ስሜት ለመጋራት በሚያስችል አለባበስ ነበር፣ አሁን ላይ ሀዘን ሲኬድ ተዘንጦ ራስን ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ግሩም ነው መቼም፡፡

ለሀሜት የሚመጡም አሉ፡፡ እገሌ ለምንድን ነው በደንብ የማያለቅሰው ፤ እገሌ ሲያለቅስ ያሳዝናል፤ እገሊት አግብታለች እንዴ ምነው ወፈረች ፤ እገሌ እና እገሌ የሆነ ነገር ጀምረዋል አሉ ....በቃ ሀሜት እንደጉድ ይፈልቃል፡፡ አንዳንዴ ሀሜቱ ሟችንም ያካትታል፡፡ እንዲህ ሆኖ ነው የሞተው ፤ እንትን ብሎ ነበር ፤ ምንትስ አድርጎ ነበር ፤ ወፍሮ ነበር ፤ ከስቶ ነበር ፤ ጠቁሮ ነበር ፤ ከእገሊት ጋ እንዲህ ነበረው ፤ ከእገሌ ጋር ተጣልቶ ነበር ወዘተ...ይሄ ሁሉ የሚወራው እዚያው ሟችን ሊቀብሩ በቆሙበት ወይም ሀዘንተኞቹ ቤት ቁጭ ተብሎ ነው። አሳፋሪ ነገር ነው፡፡ የበለጠ አሳፋሪው ነገር ሟች ታዋቂ ከሆነ የሟች ቤተሰቦች ይህን ሀሜት ትንሽ ቆይቶ በዩቲዩብ ይሰሙታል፡፡ ምን ያህል ስሜትን የሚጎዳ እንደሆነ መገመት ቀላል ነው፡፡

ሰው ሲሞት ሀይማኖቱን እና ብሄሩን የሚጠይቁ ጉደኞችም አሉ፡፡ ገና ሟች አፈር ሳይቀምስ ሀይማኖቱን ያጣሩና ከእነሱ ሀይማኖት ውጭ ከሆነ መጨረሻው ሲኦል መሆኑን ደምድመው የሚናገሩ ግብዞች ብዙ አሉ። ይህ በተለይ ለሟች ቤተሰብ በቁስላቸው ላይ እንጨት የመስደድ ያህል ነው፡፡ ነውርም ነው፡፡ በኢትዮጵያዊ ባህላችን መሰረት ሰው ሲሞት ማንም ይሁን ማን የመጀመሪያው ስራ ማዘን ነው፡፡ እናት አባቶቻችን እንኳን ለሚያውቁት ለማያውቁት ሰው ሁሉ ያለቅሱ ነበር፡፡ ለቅሷቸውም አንድም ስለሟች ነው አንድም ነግ በኔ በሚል ስሜት ነው እንጂ ራሳቸውን በማጽደቅ አይደለም፡፡ ከአንደበታቸው የሚወጣቸው ብቸኛ ቃልም ነፍስ ይማር የሚል ብቻ ነው፡፡ ዛሬ ላይ ግን ሰው ሲሞት ጥቅስ አንጠልጥሎ ለአተካሮ በየሶሻል ሚዲያው መሮጥ ፋሽን ሆኗል፡፡ ሌሎች ደግሞ ሟቹን ከአንድ ብሄር ወይም የፖለቲካ ቡድን ጋር በማያያዝ እነሱ ብቻ የማዘን መብት እንዳላቸው እና ሌሎችን ለሟች የማዘን መብት እንደሌለው ያሳስባሉ፡፡ ነውር ነው፡፡ ማን ለማን ማዘን እንዳለበት መወሰን አግባብም አይደለም፡፡ እገሌ ሲሞት ሳታለቅሱ ለእገሌ ለምን አለቀሳችሁ የሚሉ የለቅሶ ኦዲተሮችም እንዲሁ አሉ፡፡ እንዲያው ብቻ ብዙ አይነት አሳፋሪ ሰዎች ተበራክተዋል፡፡

እነዚህ ልምምዶች መስተካከል አለባቸው፡፡ ለቅሶ ላይ ካሜራ መደቀን ፤ ተኳኩሎ የግል ትርኢት መስራት ፤ ለቅሶን ለሀሜት ማራገቢያ መጠቀም ፤ በሟች ሞት ላይ የግል ሀይማኖት እና የፖለቲካ አጀንዳን ለማስፈጸም መጠቀም ያልነበረ አሁን የመጣ አዲስ ባህል ነው፡፡ ሊታረም ይገባል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ከችግሮቻችን በላይ የሆኑ ሀሳቦችና እውቀቶች ያስፈልጉናል

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ችግሮች እስካሉ ድረስ መፍትሄዎች ሁሌም አሉ። መፍትሄዎቻችን ዋጋ እንዲያመጡልን ግን ከችግሮቻችን መላቅ አለባቸው። ከችግሩ ያልበለጠ ሀሳብ፣ ያልበለጠ እውቀት ዋጋ አይኖረውም። ጨለማ በብርሀን እንደሚሸነፍ ሁሉ ችግሮቻችንም በመፍትሄዎቻችን የሚሸነፉ ናቸው። ከችግሮቻችን ለመላቅና መፍትሄ ለማምጣት መጀመሪያ የችግሮቻችንን መነሻ ምንጭ ማወቅ አለብን። አሁን ላይ ያሉብንን ሀገራዊ ችግሮች ለመቅረፍ ከመነጋገራችን በፊት የችግሮቻችንን መነሻ ምክንያት መረዳት ይኖርብናል።

ብርሀን የመልካም ነገር መገኛ ነው ፤በተቃራኒው ጨለማ ደግሞ የክፉ ነገር አብራክ ነው ። ችግሮቻችንን ለማሸነፍ ብርሀናዊ ሀሳብና እውቀት ያስፈልጉናል። ህይወት በብርሀን ውስጥ ደስ ትላለች፣ መኖር በተስፋ ውስጥ ያጓጓል። መልካም ነገር የምንመኝ ብዙዎች ነን ግን መልካም ነገር እንዴትና የት እንደሚገኝ አናውቅም። ዝም ብለን የምንፈልግ፣ ዝም ብለን የምንመኝ ነን። እዚህ አለም ላይ ካለ ፍለጋ፣ ካለ ልፋት ዝም ብሎ የሚገኝ መልካም ነገር የለም።

የምንፈልጋቸውን የሰላምም ሆኑ የአንድነት አማራጮች እንዴት ማግኘትና እንዴት ጠብቆ ማቆየት እንዳለብን ማወቅ አለብን። አብዛኞቻችን ጨለማ ውስጥ ተቀምጠን ብርሀን የምንናፍቅ፣ ሳንሰራ መብላትን፣ ሳንለፋ መልካም ህይወትን የምንሻ ነን። ለዚህም ነው እስካሁን ድረስ በነጋልን ማለዳ ላይ ጥሩ ነገር ሳንሰራ አመሻሽ ላይ የቆምነው። ለዚህም ነው ሰላም አጠገብ ቆመን ሰላም የራቀን።

እንደ ሀገር እንደ ዜጋ የእርስ በርስ ፍቅራችንን ያወየቡ በፖለቲካ እድፍ የቆሸሹ በርካታ ትላንትናዎችን አሳልፈናል። እነዚህ ትላንትናዎች ዛሬን እንዲመሩ መፍቀድ የለብንም። የትላንት የፖለቲካም እድፎችን በእርቅና በመነጋገር ፈተን ወደ ብርሀናማ ነገ መራመድ አለብን። ሰው የሚያስብ ፍጥረት ነው.. ማሰብ እውነት የሚሆነው ደግሞ በተግባር ሲገለጥ ነው። ተግባሮቻችን ነፍስ የሚዘሩት ተነጋግረን ስንስማማና የትላንት ችግሮቻችንን በእርቅ እልባት ስንሰጣቸው ነው።

ያኔ ሰውና ሀሳቡ ጥቅም መስጠት ይጀምራሉ። ሰው ለራሱም ሆነ ለሌላው ጥቅም የሚሰጠው ሀሳቡን ተጠቅሞ በጎ ነገር ሲሰራ ነው። በሀሳባችን በጎ ነገር መፍጠር ይኖርብናል። የትላንት ጨለማዎቻችን የተፈጠሩት በጎ ሀሳብ በሌለን ጭንቅላታችን ነበር። የትላንት ጨለማዎቻችን የዛሬ ብርሀናችንን እንዳይወርስብን በሃሳባችን በጎ ልንሆን ይገባል። ተነጋግረን መግባባት፣ ተነጋግረን መስማማት ይኖርብናል።

ሰው በሀሳቡ ችግሮቹን ማሸነፍ ካልቻለ፣ ጨለማዎቹን ወደ ብርሀን መቀየር ከተሳነው፣ ከወንድሞቹ ጋር ተነጋግሮ መግባባት ካልቻለ ከነውጥ ፈጣሪነት ሌላ ምንም ሊባል አይችልም። በሀሳቦቻችን ችግሮቻችንን መፍለጥ ጨለማዎቻችንን መግለጥ አለብን። የትላንት ችግሮቻችን፣ ነውሮቻችን ዛሬን እንዳንኖር ካደረጉን አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንዳለን ማሰብ እንችላለን።

ሀገራዊ ችግሮቻችን በሀገራዊ እሳቢዎቻችን የተፈጠሩ ናቸው። መፍትሄ የሚያገኙትም በሀገራዊ ተግባቦት ነው። ፖለቲካዊም ሆነ ማህበራዊ ተግዳሮቶቻችን ከየትም የመጡ ሳይሆኑ እኛን ታከው፣ እኛኑ ተደግፈው ነፍስ የዘሩ ናቸው። እኚህ ችግሮቻችን እልባት እንዲያገኙ ችግር ፈጣሪ ሀሳቦቻችን ወደ መፍትሄ ፈጣሪነት መመለስ አለባቸው። በትችት፣ በወቀሳ፣ በእርግማንና በአሉባልታ ያለፈ ጊዜአችን ሀገር ወደመጥቀም፣ ለሀገር ወደመልፋት መዞር አለበት።

እኛ ለራሳችን በቂዎች ነን። መነጋገር ከቻልን ብዙ ሀሳብ፣ ብዙ እውቀት ያለን ህዝቦች ነን። ሀገራችን ተስፋ በጣለችበት በሀገራዊ ምክክሩ ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮቻችንን ማሸነፍ እንችላለን። ጨለማዎቻችንን ወደ ብርሀን መለወጥ ይቻለናል። ትላንት ምንም ይሁን እኛ ለአንድነትና ተነጋግሮ ለመስማማት ከበረታን ችግሮቻችን አይበልጡንም። ችግሮቻችን እየበለጡን ያሉት እኛ ከችግሮቻችን ስላነስን ነው። እስከዛሬ ዝቅ ያልነው ከፍ የሚያደርግ የአንድነት ሀሳብ አጥተን ስለኖርን ነው። ከችግሮቻችን ስላነስን ነው።

ዘመኑ የስልጣኔና የአንድነት ነው። በሀሳባችን ሌሎችን ማሸነፍ ካልቻልን ሌሎችን ልናሸንፍበት የምንችልበት ምንም እድል የለንም። ለራሳችንም ሆነች በብዙ ነገሯ ለተራቆተችው ሀገራችን የሚበጃት ዘመኑን የዋጀ ሀሳብና ተግባቦት ነው። በዚህ ዘመን ላይ ተፈጥረን በጋራ ጉዳያችን ላይ በጋራ ተነጋግረን ካልተግባባን የሌሎች መሳቂያ ከመሆን ውጪ ምንም አናተርፍም። ራሳችንን መፍጠር አለብን..በሀሳባችን፣ በአንድነታችን የተሰፈረ ጸጋችንን፣ የተሰወረ ክብራችንን ማግኘት አለብን።

ሰው ተነጋግሮ ካልተግባባ ሰውነቱ እዛ ጋ ያበቃና አውሬ መሆን ይጀምራል። ከአውሬነት የሚያወጣን ሀሳብ ብቻ ነው። ሀሳብ ስላችሁ ግን ተነጋግሮ በማሸነፍና ተግባብቶ በመሸነፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ማለቴ ነው። እንዲህ ካልሆነ ሰውነት ምንም ነው። ተነጋግሮ መስማማት ከምንምነት መውጫ መንገዳችን ነው። የዘመናት የእምነታችን ሚስጢር ሀሳብ ማጣታችን ሳይሆን ላለመስማማትና ላለመሸነፍ መነጋገራችን ነው። ሰው የሚነጋገረው በተሻለ ሀሳብ ችግሮቹን ለማሸነፍ። በተሻለ ሀሳብ መፍትሄ ለማምጣት፣ በተሻለ ምክረ ሀሳብ ወደፊት ለመራመድ ነው። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ ውስጥ ሌላ እምነትን በራስ ላይ ከማከል ውጪ የሚፈጠር ተዐምር የለም።

ትላንትን እንርሳው..ወደሚያግባባን አንድ ወደሚያደርገን የጋራ እውነት እናምራ። ባለመነጋገር የፈጠርናቸው ጨለማዎች ዛሬ እንዲያበቁ አስታራቂ ሀሳቦችን እናዋጣ። ችግር ከመፍጠር ወደመፍትሄ አመንጪነት እንሸጋገር። በጋራ ሀሳብ የጋራ ህልም እንትለም። ወደ ነገ..ወደ አዲስ ቀን፣ ወደ ተሻለ ከፍታ ሊያራምደን በሚችል ጉዳይ ላይ ጊዜና እውቀታችንን እንገበር። ትላንት ላይ በእውቀት..በአስተሳሰብ የተሻልን ብንሆን ኖሮ ዛሬ ላይ እነዚህ ሁሉ ስቃዮቻችን ባልነበሩ ነበር። ስቃዮቻችንን በእርቅ እንግደላቸው።

ጉስቁልናዎቻችንን በምክረ ሀሳብ እናሸንፋቸው። ሁሉንም ሞክረው የቀረን መግባባት ነው..መስማት ነው። እስኪ እንስማማና ያልደረስንበትን ከፍታ እንድረስበት። የማንፈልገው ነገ እንዳይፈጠር በምንፈልገው ዛሬ ላይ መሆናችንን ልብ ልንል ይገባል። የማትፈልጉት ነገ እንዳይፈጠር በምትፈልጉትና በሚያስፈልጋችሁ ዛሬ ላይ መሆናችሁን ልብ በሉ። ዛሬ የእኔና የእናንተ የትላንት መልክ ነው..አስተሳሰባችን ነው የፈጠረው። ነጋችን የተሻለ እንዲሆን ከትላንቱ የተሻለ ሀሳብ፣ እውቀት፣ ተግባቦት ያስፈልገናል።

የህይወታችን ብሎን የሀገራችን አናጺዎች እኛ ነን። ትውልዱ የሚገነባው ዛሬ እኛ በምንሆነው መሆን ነው። ለምንም ነገር መልካም ልብ ያስፈልገናል። መልካም ልብ በውስጡ ነውር የለውም። ሰውነታችንን የሚፈጥሩት ልቦቻችን ናቸው። መልካም ልብ ካለን ያለጥርጥር መልካም ዜጋ መሆን እንችላለን። መልካም ዜጋ ደግሞ መገለጫው ፍቅርና አንድነት ነው። እናም ልቦቻችንን ለበጎ ሀሳብ እናስገዛ።

ከፊታችን ያሉ ሀገራዊም ሆኑ ግለሰባዊ ተስፋዎች አብበው የሚለመልሙት በእኛ ልብ ላይ በእኛ ሀሳብ ተዘርተው ነው። ልቦቻችን ጭንጫ ከሆኑ..ሀሳቦቻችን ጭንጋፍ ከሆኑ መልካም ዘር አያበቅሉም። መልካም ፍሬ አይሰጡንም። ልባችን ሰላሳና ስልሳ መቶም የምናፈራበት ማሳችን ነው። ሀሳባችን ደግሞ ዘር። በልባችን ማሳ ላይ መልካም ፍሬ እንድንበላ በመልካም ልብ ውስጥ የበቀለ መልካም ሀሳብ ያስፈልገናል። የሚጠቅመን ይሄ ነው..በመልካም መሬት ላይ መልካም ዘርን መዝራት። ዛሬ ላይ እያሰቃዩን ያሉት በአዳፋ ልብ ላይ በአዳፋ ሀሳቦቻችን የዘራናቸው ዘሮች ናቸው። እኚህ እኩይ ዘሮች እንዲደርቁ.. እንዲጠወልጉ ሀሳብ ያስፈልጋል..የእርቅና የተግባቦት ሀሳብ።

ማንም ገሎን አያውቅም..ማንም ክፉ ሆኖብን አያውቅም። ማንም አጠገባችን ደርሶ አያውቅም ችግሮቻችን ሁሉ ሀገር በቀል ናቸው..በክፉ ልብ ላይ በክፉ ሀሳብ የተዘሩ። ላለመግባባት እየተሰበሰብን፣ ላለመስማማት እየተነጋገረን እንዴት ነው ሀገርና ህዝብ የምንገነባው? እንዴት ነው ከጥላቻና ከመገፋፋት የምንወጣው? እንዴት ነው ከህልማችንና ከተስፋችን ወደብ የምንደርሰው? መጀመሪያ ልቦቻችንን መልካም እናድርግ ። የትም መቼም የህይወታችን አድማቂዎችም አደብዛዦችም እኛ ነን። ከእኛ ውጪ እኛን ሊረዳ፣ እኛን ሊታደግ፣ ከጨለማ ሊያወጣን የሚችል ሀይል የለም።

> ትላንትን በመድገም፣ ካለመፍትሄ ችግሮቻችንን ብቻ እየመላለስን በመነጋገር የሚመጣ ለውጥ..የሚመጣ ብርሀን የለም። ብርሀን ከጨለማ ቀጥሎ የሚመጣ ነው..ብርሀን እንዲመጣ ጨለማ ገለል ማለት አለበት። ባልተኖረ ዛሬ፣ ተስፋቢስ በሆነ አሁን ላይ ቆመን ታላቅ ነገን መገንባት አንችልም። ሀሳቦቻችንን እንባርክ.. ለብርሀናችን ጨለማዊ አስተሳሰባችንን ገለል እናድርግለት።

ሀይላችን ያለው መግባባታችን ውስጥ ነው። ህልምና ራዕዮቻችን የተቀመጡት በመስማማታችን ውስጥ ነው። መልካም ነገ እንዲኖረን መልካም ዛሬ ያስፈልገናል። ነገ እኮ በዛሬ አስተሳሰብ፣ በዛሬ ብርሀን የሚፈጠር እንጂ እንዲያው ዝም ብለን ከመሬት ተነስተን ተስፋ የምናደርገው ነገር አይደለም። ከዚህ ውጪ ሌላ ሰዋዊም ሆነ አምላካዊ ቀመር የለም። ተፈጥሮ በእኛ ቁጥጥር ስር ነው። በተፈጥሮ ላይ የበላይ ሆነን ነው ወደዚህ አለም የመጣነው። በአስተሳሰባችን መልካሞች ከሆንን የሚያሸንፈን ምንም ነገር የለም የውድቀታችን..የተስፋቢስነታችን መነሻም መድረሻም በውስጣችን አዎንታዊ አስተሳሰብ አለመኖር የፈጠረው ነው።

ይሄ አለም በአምላክ አስተሳሰብ ተፈጥሮአል በእኛ አስተሳሰብ ይቀጥላል። ብዙ ነገዎች ብዙ ዘላለማት ከፊታችን አሉ። እልፍ ንጋቶች እልፍ ምሽቶች ይጠብቁናል። ሁሉም ነገር በእኛ ቁጥጥር ስር ነው በጨለማ እየኖርን የምንፈጥረው ብርሀናማ ነገ የለም። በቁጭትና በጸጸት እየኖርን አዲስነትን መላበስ አይቻለንም። ተነጋግረን መስማማት ከቻልን አሁኑኑ ተዐምራቶቻችንን መፍጠር እንችላለን። ተምረን የከሰርነው፣ ሀይልና ጉልበት እያለን ጠባቂ የሆነው፣ ውድ ጊዜአችንን በከንቱ የምናሳልፈው በውስጣችን ለለውጥ የሚሆን ተነሳሽነት ስለሌለን ነው።

በማሰብ..በማሰላሰል፣ በእርቅና በተግባቦት በበላጭ እውነት ከጨለማ እስካልወጣን ድረስ ሀገራችንም ሆነ ህዝባችን መልካም ነገን ማየት አይቻለውም። በፍቅርና በአንድነት ተዐምራችንን መፍጠር ካልቻልን ተአምር የሚፈጥርልን ማንም ሀይል የለም። የተዐምራት ሀይል ያለው በፍቅርና በአንድነት ሀይል ውስጥ ነው። በመነጋገርና በመስማማት ውስጥ ነው። የፈጣሪ አይኖች እንኳን በልበ ብርሀኖች ላይ ናቸው። ለራሳችን፣ ለክብራችን፣ ለሀገራችን፣ ለሚመጣው ጊዜ ዋጋ ካልሰጠን ጨለማ ውስጥ ለመኖር ፈቅደናል ማለት ነው።

ትላንትን በመድገም፣ ካለመፍትሄ ችግሮቻችንን ብቻ እየመላለስን በመነጋገር የሚመጣ ለውጥ.. የሚመጣ ብርሀን የለም። ብርሀን ከጨለማ ቀጥሎ የሚመጣ ነው..ብርሀን እንዲመጣ ጨለማ ገለል ማለት አለበት። ባልተኖረ ዛሬ፣ ተስፋቢስ በሆነ አሁን ላይ ቆመን ታላቅ ነገን መገንባት አንችልም። ሀሳቦቻችንን እንባርክ..ለብርሀናችን ጨለማዊ አስተሳሰባችንን ገለል እናድርግለት። አለም ያስደነቀንና እያስደነቀን ያለው በተግባቦት ሀሳብ ነው። አለም ላይ ካለአንድነትና ካለተግባቦት ሀሳብ የሆነ የለም።

ሀሳብ ከአንድ ሰው ሊነሳ ይችላል ያ ሃሳብ ዋጋ እንዲያገኝ ግን በዙሪያው በርካታ ሀሳቦች ሊከቡት ይገባል። እኛ ሀገር ይሄ እውነት የለም.. ስብሰባ የምንቀመጠው ተነጋግረን ለመግባባት ሳይሆን ተነጋግረን ለመለያየት ነው፣ ተነጋግረን የበላይነታችንን ለማሳየት ነው። ይሄ አስተሳሰብ ነው ዛሬ ላይ ጨለማን የጋረጠብን። ይሄ አስተሳሰብ ነው አለም ጥሎን እንዲሄድ ያደረገው። ከድጥ ለመውጣት ብዙዎቻችንን ያስማሙ፣ ያግባቡና ይሁንታ የተቸራቸው ሀሳቦች ያስፈልጉናል።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅም እስከዛሬ በራሳችንም ሆነ በሀገራችን ላይ ብዙ ስህተቶችን ሰርተናል። የነዛ ስህተቶቻችን ማብቂያ ቀን ሳይታወቅ ነውሮቻችንን አቅፈንና ደግፈን እሹሩሩ ስንል ኖረናል። አሁን ነውሮቻችንን ገለን ቀብረን የምንፈልገውን ህይወት፣ የምንፈልገውን ከፍታ የምናይበት ጊዜ እንዲሆን መበርታት አለብን። በችግሮቻችን ተበልጠን፣ ለመፍትሄ ሳይሆን ለጥፋት በርትተን የኖርንባቸው ጊዜዎች አብቅተው በእርቅና በምክክር አዲስ ተስፋን የምንሰንቅበት የመታደስ ጊዜ እንዲሆን ሀሳብ ማዋጣት አለብን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# በተለያዩ የግብርና ዘርፎች ክረምት ከበጋ ውጤታማ ለመሆን እየተከናወነ ያለ ተግባር

ስምስም መንግሥቱ

በዚህ ክረምቱ ለበጋው ተራውን እየለቀቀ ባለበት በአሁኑ ወቅት ወደ ገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ወጣ ያለ መንፈሱ ሁሉ ይታደሳል። የደረሰው ሰብል በንፋስ ኃይል ሲዘናፈል፣ ከብቱ በየመስኩ ተሰማርቶ ለምለሙን ሳር ሲግጥ፣ በክረምቱ ደፍርሶ ሲያስፈራ የቆየው ወንዝ ሰከን ብሎ ውሃው ጥርትና ኮለል ብሎ ሲወርድ ይመለከታል። የአየሩ ነፋሻነት፣ የሜዳ ሸንተረሩ በአበባ በለምለም ሳር መድመቅ ሌላው የገጠሩ ክፍል የዚህ ወቅት ትዕይንት ነው። በተለይ ሰብሉን ሲያይ አይኑ ይጠግባል።

አዝመራ ከማሳ ተሰብስቦ ጎተራ እስከሚገባ አይነገርም በሚለው ብሂል እንጂ በቅርቡ ለሥራ ጉዳይ ወደ ገጠሩ ክፍል በሄድኩበት ወቅት በአለፍ ገደም እንደተመለከትኩትም፣ ከአንዳንድ አርሶ አደሮች እንደሰማሁትም በማሳ ላይ ያለው የመኸር ወቅት ሰብል አያያዝ አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ይዞታው ጥሩ ነው። ገበሬው እንዲህ ያለ ተስፋ ከማሳው ሲመለከት ከወዲሁ ያጠግባል።

በአሁኑ ወቅት ያለው የኢትዮጵያ የግብርና ሥራ እንደ ቀደመው ጊዜ ወይንም ኋላቀር የግብርና ዘዴ እየተባለ ሲገለጽ እንደነበረው አይደለም። በክረምቱ ወይም በመኸሩ የተዘራውን ሰብል ለመሰብሰብ ከመዘጋጀት ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ሥራ ይቀጥላል፤ ከዚያ ደግሞ በልግ ይመጣል፤ በመሆኑም በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡና ተክል በሁሉም ልማቱን የማጠናከር ሥራ እንደ ሀገር ተጠናክሯል።

በቅርቡ ለሥራ ጉዳይ ሲዳማ ክልል በንሳ ወረዳ በተገኘሁበት ወቅት ከአካባቢው የተለያዩ ወገኖች እንደተረዳሁት፤ አካባቢው ሰብል አምራች ብቻ ሳይሆን፣ በቡና ልማትና በእንስሳት ሀብትም ይታወቃል።አርሶ አደሩ በነዚህ ሁሉ አማራጮች በመጠቀም ኑሮውን እንዲያሻሽል፤ በአካባቢውና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ከክልሉ አመራር ጀምሮ እስከታች ባለው መዋቅር የተናበበ ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው።

ለዚህም የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል የወተት ላሞችን ምርታማነት ለመጨመር እየተደረገ ያለው ጥረት አንዱ ማሳያ መሆኑን ተመልክቻለሁ። በወረዳው ስለምርት ዘመኑ የግብርና ሥራ እና ስለሚጠበቀው ምርት፣ ለበጋ መስኖ ልማት እየተደረገ ስላለው ዝግጅት ከበንሳ ወረዳ ዋና አስተዳደሪ አቶ ዘነበ ባናታ ጋር ቆይታ አድርጌያለሁ።

### በእንስሳት ልማት

አቶ ዘነበ እንዳስረዱት፤ በቤተሰብ ደረጃ የአርሶ አደሩን ኑሮ ማሻሻል (ብልጽግና ማምጣት) የሚቻለው በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በቡና ልማትና በከብት እርባታ ሁለገብ የሆነ የግብርና ሥራ በማከናወን ነው። ክልሉም ሆነ ወረዳው በዚህ መንፈስ በልማቱ ላይ በትኩረት እየሠሩ ይገኛሉ።

በእንስሳት ልማቱ የሀገረሰብ ከብትን ከውጭ ዝርያ ጋር በማዳቀል ምርታማነትን ለማሳደግ በተለይም በወተት ምርታማነት ላይ እየተከናወነ ባለው ሥራ ወረዳው ውጤታማ ተግባር እያከናወነ ነው። ለውጤቱ ወረዳው አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ሥራ ሲሠራ፣ አርሶ አደሩ ደግሞ ፍቃደኝነቱን አሳይቷል። በዚህ መልኩ የተናበበና የተቀናጀ ሥራ ማከናወን ተችሏል።

የወረዳው ሥራ በዚህ ረገድ አርሶ አደሩ ዝርያቸው ለተሻሻለ እንስሳቱ በቂ መኖ ለማቅረብ እንዲችል ለመኖ ማልሚያ ወደ አንድ ሺ ሄክታር መሬት ምቹ በማድረግ፣ የተመጣጠነ የመኖ አዘገጃጀት ዘዴን እንዲጠቀምም በወረዳው ባለሙያዎች በማገዝ፣ በ24ቱም የወረዳው ቀበሌዎች የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ኬላዎችን በማመቻቸትና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በማሟላት ይገለጻል።

### በቡና ልማት

ወረዳው በቡና ልማትም ይታወቃል ያሉት አቶ ዘነበ፣ ከወረዳው 24 ቀበሌዎች ከአንዱ ቀበሌ በስተቀር ሁሉም ቡና አብቃይ መሆናቸውን ያመለክታሉ። አስራ ስድስት ሺ ሶስት መቶ አስራ አምስት (16ሺ315) ሄክታር



አቶ ዘነበ ባናታ፤

መሬት በቡና ተሸፍኗል፤ ከዚህ ውስጥም አስራ አምስት ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ ሶስት (15353) ሄክታር የሚሆነው ምርታማ ነው።

በወረዳው 53 የቡና ኢንዱስትሪዎችም ይገኛሉ። አርሶ አደሩ በኩታ ገጠም የግብርና ዘዴ እንዲጠቀም ፣ የጥላ ዛፍ ችግኞችን በመትከል፣ ማዳበሪያ በማቅረብ፣ ወቅቱን ጠብቆ ጉንደላ በማካሄድና ሌሎች ምርታማነትን የሚጨምሩ ወደ 11 የሚሆኑ ግብዓቶችን (ፓኬጆች) በማቅረብና የባለሙያ እገዛ በማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

ከቡና ጉንደላ ጋር ተያይዞ ይነሳ የነበረውን ችግር ለማስቀረትም ወረዳው እንቅስቃሴ ማድረጉንና ከጉንደላ ባለፈም ምርታማ ያልሆነውን ቡና ነቅሎ ጥሎ በሌላ በመተካት ጭምር በወረዳው ሰፊ ተግባራት ተከናውነዋል። በወረዳው ብቻ ወደ ሶስት ሺ የቡና እግር ተነቅሎ በአዲስ ተተክቷል። 358 ሄክታር የቡና ተክል ተጎንድሏል።

እስካሁን ባለው የቡና ልማት ሥራ በወረዳው በሄክታር 10 ኩንታል የቡና ምርት እየተገኘ ነው። ሞዴል የሚባል አርሶ አደር ግን እስከ 20 ኩንታል የሚያገኝበት ሁኔታም አለ። በሞዴል አርሶ አደርና በሌሎች መካከል የሚገኘው የምርት መጠን የሚለያይ በመሆኑ ይህን ማመጣጠንና ከፍተኛ ምርትም ለማምረት የበለጠ መሥራት ይጠበቃል። በዘንድሮ የምርት ዘመን በሄክታር 13 ኩንታል ለማግኘት እየተሠራ ነው። ቡና ከሚሰጠው የምርት መጠን አንጻር ብዙ እንዳልተሠራ አቶ ዘነበ ይናገራሉ።

በወረዳና በክልል ደረጃም በታዩ ጉድለቶች እና የመፍትሔ ሀሳቦች ላይ በመነጋገር ምርታማነት ላይ ጠንክሮ ለመሥራት ከመግባባት መደረሱን አስታውቀዋል። አርሶ አደሩ በሚያገኘው ጥቂት ምርት ረክቶ እንዳይዘናጋ የግብርና ኤክስቴንሽንን በማጠናከር ረገድ የልማት ሠራተኛው ውሎና አዳሩን ከአርሶ አደሩ ጋር በማድረግ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል በማድረግና በማንቃት የበለጠ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ከቁጥጥር ውጭ የሆነው የአየር ንብረት መዛባት ለምርታማነት መቀነስም የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህን መከላከል የሚቻለው ጥላ ዛፍ በሰፊው በመትከል ነው። አርሶ አደሩ ይህን እንዲያከናውን የኤክስቴንሽን ባለሙያው ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማድረግ ይገባል።

ሌላው የቡና ምርታማነትን የሚቀንሰው በሽታና ተባይ ነው። በተለይም ፍሬውን የሚያራግፍ በሽታ እየተከሰተ ነው። በዚህ ላይም ተከታታይ በሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለችግሩ መፍትሄ እንዲገኝ ማድረግ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ የወረዳው አመራር የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት በትኩረት እየሠራ ይገኛል። በቡና ልማቱ ላይ እነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ቢኖሩም፣ ከሌሎች የክልሉ ወረዳዎች ጋር በንጽጽር ሲታይ በንሳ ወረዳ በተሻለ ቡና አምራች እንደሆነ አመልክተዋል።

በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ ላይ በተካሄደው የሽልማት መርሐ ግብርም የሽልማት መስፈርቱን አሟልተው ከተሸለሙት መካከል የበንሳ ወረዳ አንዱ እንደሆነም ጠቅሰዋል። በቡና አያያዝ፣ ከምርታማነት፣ ከግብይት አንጻርም የተሻለ አፈፃፀም በማስመዝገብ ከሌሎች ተሽሎ መገኘቱ ለሽልማት ካበቁት ምክንያቶች መካከል የሚጠቀስ እንደሆነ ነው ያስረዱት። የተገኘው የሜዳሊያ ሽልማት የበለጠ ምርታማ እንዲሆኑ እንደሚያስችላቸውና ከተሠራ የበለጠ ሽልማት እንደሚገኝም ተናግረዋል።

### በሰብል ልማት

በወረዳው በሰብል ልማት በ2014-2015 የምርት ዘመን በተከናወነው የመኸር ግብርና ሥራ ሶስት ሺ አራት መቶ አስራ አንድ (3411) ሄክታር መሬት በተለያየ የሰብል ዘር ለመሸፈን ከተያዘው እቅድ ወደ ሶስት ሺ አምስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ (3569) ሄክታር መሬት በተለያየ ዘር በመሸፈን እቅዱን ለማሳካት ተችሏል።

በወረዳው ዋና ዋና ሰብሎች ይለማሉ፤ ከእነዚህ መካከልም ጤፍ፣ቦሎቄ፣ስንዴና ገብስ ይጠቀሳሉ።ምርትማነቱም ከሰብል ሰብል ይለያያል። ለአብነትም ጤፍ በሄክታር 18 ኩንታል ይገኝ የነበረውን ወደ 20 ኩንታል፣ በሄክታር 38 ኩንታል ይገኝ የነበረውን የገብስ ምርትም ወደ 44 ኩንታል ከፍ ለማድረግ ታቅዷል።

በዚህ መንገድ በአጠቃላይ ሰባት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሶስት (769833)ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ነው እየተሠራ ያለው። የአየሩ ሁኔታም ለእርሻ ሥራው ጥሩ በመሆኑና የሰብል ይዞታውም መልካም በሚባል ደረጃ ላይ ስለሚገኝ እቅዱ ይሳካል የሚል እምነት ተይዟል።

ወረዳው ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች አሉት። አርሶ አደሩ ወቅታዊው የኑሮ ውድነት ብዙ ያስተማረው በመሆኑ ምርታማነትን በማሳደግ ለራሱም ሆነ ለሸማቹ በቂ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ተግቶ እየሠራ ይገኛል። ከመኸሩ በፊት በነበረው የበልግ ወቅት ለግብርና ሥራው ተስማሚ የአየር ፀባይ ባለመኖሩ ዝቅተኛ ምርት ነው የተገኘው። በተለይም በቆሎ ገና አንዱንም ሳይዘው ጠፍቷል።

አካባቢው በሰብል ልማት የሚታወቀው በበቆሎ ልማት ነው ስለሚባለውም አቶ ዘነበ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ በቆሎ በቆላማው አካባቢ ወደ ሰባት ያህል በሚሆኑ ቀበሌዎች በስፋት ይመረታል። የበቆሎ ምርት ሲነሳ ጤፍ ይዘራበታል። ወደ ደጋው ደግሞ ስንዴና ገብስ ይለማል።በአጠቃላይ በወረዳው ብርዕ እና ጥራጥሬ ሰብሎች ይለማሉ።

በመኸሩ የተከናወነው የግብርና ሥራ ወደ መጠናቀቁና ምርት ወደ መሰብሰቡ እየተቃረበ ነው።ቀጣዩ የበጋ መስኖ ልማት ነው። ከዚህ አንጻር ወረዳው እያከናወነ ስላለው ተግባር አቶ ዘነበ እንዳስረዱት፤ በክልል ደረጃ በተደረገው ዝግጅት አቅጣጫ ወርዶ በወረዳው በበጋ መስኖ አንድ ሺ ሄክታር መሬት ለማልማት ወደ ሥራ ተገብቷል።

የመስኖ ልማቱ በአጭር ጊዜ በሚደርሱ ምርቶች እንደ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ባሉት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ቢሆንም፣ ሌሎች ሰብሎችም እንዲለሙ ይደረጋል። የትኛው መሬትና ውሃ ለጥቅም ይውላል፣በውሃ መሳቢያ መሣሪያ (ጀነሬተር) ነው ወይንስ ውሃ በመጥለፍ ነው ሥራው የሚሠራው፣ማንስ ምን ይጠቀማል የሚለው የልየታ ሥራ ቀድሞ ተከናውኗል።

በወረዳው ቆላማ ክፍል የበቆሎ ምርት በመነሳቱ ለበጋው ልማት የመሬት ዝግጅት ተጀምሯል።የመኸሩ ምርት ሲነሳ ከስር ከስር የበጋው ልማት ሥራ ይቀጥላል። ለመስኖ ልማት አስፈላጊ የሆነው የውሃ አቅርቦትም በወረዳው ላይ እንደ ችግር እንደማይነሳም አመልክተዋል። ውሃ ከከርሰ ምድር የማውጣት አማራጭ በመኖሩም፣ ይህንንም በመጠቀም አነስተኛ የእርሻ መሬትም ቢሆን ለልማት እንዲውል የማድረግ አቅጣጫ ተይዟል።

የእርሻ ሥራው በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን የሜካናይዜሽን አጠቃቀምን በተመለከተም ሲገልጹ በዚህ ረገድ ወረዳው ገና ይቀረዋል ነው ያሉት። የመሬት አቀማመጡና የተበጣጠሰ የእርሻ ማሳ መኖሩ ለሜካናይዜሽን ምቹ እንዳይሆን አንዱ ምክንያት መሆኑም ትኩረቱን አናሳ አድርጎታል ይላሉ። ግን ደግሞ ወደፊት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ ወደቴክኖሎጂው ይገባል ብለዋል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚሠራው ሥራ የአርሶ አደሩን ኑሮ መቀየርና የኑሮ ውድነትን ማረጋገጥን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አንጻር ወረዳው ክረምት ከበጋ በማምረት ስላለው ቁርጠኝነትም አቶ ዘነበ ሲገልጹም  የተያዘው አቅጣጫ በገጠሩ ብቻ ሳይሆን የከተማ ግብርናን በማከናወን እየተፈጸመ መሆኑን ተናግረዋል። አርሶ አደሩ ቀደም ሲል የማይጠቀምባቸውን ቦታዎች ሁሉ ለልማት በማዋል እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ የግብርና ሥራውን በትኩረት መሥራት ግዴታ መሆኑን ነው ያመለከቱት። የወረዳ አስተዳዳሪው እንዳሉት፤ የሀገር ኢኮኖሚ እድገት መሠረት የሆነውን የግብርና ሥራ ማጠናከር ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።

## ማህበራዊ
# አስኳላ

# አዲሱ የትምህርት ስርዓት ምን ይዟል?

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ከ1986 በፊት በነበረው የትምህርት ስርዓት የተማሪዎችን የወደፊት ጉዞ ሚቃኑና የዕለት ተዕለት ኑሯቸውን በቀላሉ መምራት የሚያስችሏቸው የትምህርት አይነቶች በስፋት ይሠጡ ነበር። በዛ ወቅት ከነበሩ ትምህርቶች ምን ታስታውሳለህ(ሽ) ቢባል ብዙው ሰው ደርሶ ካየው የእጅ ሥራንና እርሻን ሳይጠቁም ያልፋል ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም እነዚህ ትምህርቶች ቤታችንን አስውበው ግቢያችን የደረሰ ውበትን ሰጥተውናል። የምንፈልገውን ተመግበንም ውስጣችን እንዲያምርም አድርገውናል። ከምንም በላይ ከጎረቤት የምንግባባበትንና የምንዋደድበትን እድል ሰጥተውናል። እንዴት ከተባለ ዳንቴልና የተለያዩ የጥልፍ ስራዎችን በመስራት ጉርብትናችንን አጥብቀናል። በእርሻ ትምህርትም ምድሪቱ ያበቀለችውን በመስጠትም እንዲሁ የእኔ ቤት የእናንተም ነው ብለናል፡፡ቀደም ባለው ጊዜ ደግሞ የግብረ ገብነት ትምህርት የዜጎችን ማንነት በመቅረጽ ረገድ የማይተካ ሚና ነበረው።

ይህ ደግሞ ዛሬ ዳግም ወደ ትምህርት ስርዓቱ ቢገባ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው። የብዙዎች እይታ ያረፈበት የቀድሞ ትምህርት ስርዓትም ለዚህ ይሆናል። ተወዳጅ፣ ተናፋቂና አገር አሳዳጊ እንደሆነ በደንብ የሚያሳይም ነው። ያው ሁሉንም ትምህርቶች ላይሆን ይችላል። ጉድለቶችም ይኖሩታል። ምክንያቱም ዛሬ ያለነው 21ኛው ክፍለዘመን ላይ ነን። ያንን የሚመጥን ሥራና ተግባር ያስፈልገናል። እናም እንደትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ሲያደርግ ቀደምቶቹንና ተወዳጆቹን ዳግም በማምጣት ከዘመኑ ጋር የሚራመዱና ተማሪን የሚገነቡ አድርጎ አዘጋጅቶታል፡፡

ተሻሻለ፣ ተከለሰ ሲባልም የቀደመውን ሙሉ ተግባር እርግፍ አድርጎ ተወ ማለት አይደለምና መሻሻልን ከዘመኑና ከነባር እውቀት ጋር አዛምዶታል። ለዚህም ማሳያው ቀደም ብለው በትምህርት ስርዓት ውስጥ ተካተው ሲሰራባቸው የቆዩት የትምህርት መስኮች ዳግመኛ በአዲሱ ስርዓትም ተካተው እንዲሰራባቸው መሆናቸው ነው። በጉዳዩ ላይ ሲሰሩ የነበሩትና በትምህርት ሚኒስቴር አሁንም እያገለገሉ ያሉት ኃላፊዎች ይህንን ያረጋግጣሉ።

የመጀመሪያው በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ማበልፀጊያ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ቴዎድሮስ ሸዋርገጥ ሲሆኑ፣ የፍኖተ ካርታ ተሰርቶ የትምህርት ስርዓት አተገባበሩ ተፈትሾ በአዲስ መልክ ለመሥራት ሲታቀድ ብዙ ስኬቶችን ለማምጣት እንደሆነ በሙከራ ትግበራ አጀማመር፣ በተዘጋጁት የማስተማሪያ መጽሀፍትና በትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ የአሰልጣኞች ሥልጠና በደብረ ብርሀን ከተማ በተከናወነበት ወቅት ተናግረዋል።

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሥርዓተ ትምህርት ሪፎርሙ ግድ መሆኑን የጠቀሱት መሪ ስራአስፈጻሚው፤ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሥርዓተ ትምህርቱ ታስቦበት እንዲዘጋጅ ሆኗል። ሰነዶችም የሚያካትታቸው የተማሪ ባህሪያት፣ የይዘት ፍሰት መርሀ ትምህርትና ሌሎች ዝግጅቶች ናቸው። በዚህ ውስጥም ፍኖተ ካርታው የተሻሻለውና አዲሱ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው በትምህርት ሥርዓቱ የመማር ማስተማሩን የጥራት ደረጃ ለማሻሻል፣ እንዲሁም ሙያዊ ግዴታውን በብቃት የሚወጣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የትምህርት ማኅበረሰብ ለመፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ ተወዳጅና ለውጥ አምጪ ትምህርቶችን በትምህር ስርዓቱ ውስጥ ማካተት ጠቃሚ እንደሆነ ያነሳሉ።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ግብረ ገብነት፣ አገር በቀል ዕውቀት፣ ሙያና የቀለም ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ ምርትና ተግባር፣ ጥናትና ምርምር ትኩረት የተደረገባቸውም ለዚህ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የሀገር በቀል እውቀት እንዲኖራቸው፤ የግብረ ገብና የሥነ- ምግባር ባለቤት እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም የሥራና ተግባር ትምህርት ተካቶ ስለሚሰጣቸው የራሳቸውን ሥራ በራሳቸው እንዲፈጥሩ እድል ይፈጥርላቸዋል። ከተቀጣሪነት ተላቀው የራሳቸውን ገቢ የሚያመነጩ ተማሪዎች ያደርጋቸዋልም ይላሉ።

በትምህርት ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶች ስርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ዛፉ አብርሃ

> **ሥነ ጥበብ ብዙ አይነት የሰው ልጅ ድርጊቶችን የሚያጠቃልል ዘርፍ ነው። እንዲታዩ ወይም እንዲሰሙ፣ እንዲወደዱ ወይም እንዲተገበሩ የምንፈልጋቸውን ነገሮች በጥበብ ኃይል በሙያው እንዲፈጸሙ የምናደርግበት ድርጊት ነው**

በበኩላቸው እንዳሉት፤ ስርዓተ ትምህርቱ በዚህ ዓመት ሙሉ እና የሙከራ ትግበራ ከተደረገበት በኋላ በ2016 ዓ.ም የሚኖሩ ችግሮችን በማስተካከል እና በማዳበር ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ የሚገባ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው። አንዱ የትምህርት አይነቶች አካታችነት ነው። ይህ ሲባልም ሥራና ተግባርን የሚያካትቱ፤ አገርን በቀላሉ የሚለውጡ የትምህርት አይነቶችን አስገብቶ ተማሪዎች እንዲጠቀሙባቸው ማድረግ ነው። ለአብነትም የእርሻ ትምህርት፤ ግብረገብና የስነጥበብና የአገር በቀል እውቀት ትምህርቶች ከፍተኛ ለውጥ ያመጣሉና ወደተግባር እንዲገባባቸው ተደርገዋል። ምን ምን ጥቅም ይሰጣሉ ከተባለ ብዙ መዘርዘር ይቻላል።

### የእርሻ ትምህርት

በልቶ ከማደር ባሻገር ገቢያችንን ከፍ ለማድረግ ስናስብ ዘመናዊ የእርሻ ሥራን መጠቀምና በእውቀት የጎለበተ እርሻን መፍጠር ግዴታችን እንደሆነ እናምናለን። ለዚህ ደግሞ እውቀት ግድ ነው። እናም እርሻን እንደ አንድ የትምህርት አይነት አድርጎ መጠቀሙ መፍትሄ እንደሚሆነን አጠያያቂ አይደለም። በእርግጥ ከዚህ ቀደም በነበረው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ እርሻ ብቻ ሳይሆን ኑሮዘዴ የሚባልም የትምህርት አይነት ነበር። ይህ ደግሞ ስንቶችን እንደለወጠ የነበሩበት ይናገሩታል። በተለይም ለአካባቢ ስነምህዳር የሚሰጡት ትኩረት ምንም መተኪያ የሌለው እንደነበረ ታሪክ ያስረዳናል።

ለምግብነት የሚሆኑ ነገሮችን ከመግዛት ይልቅ ከጓሯቸው፤ አለፍ ሲልም ከትምህርትቤት ቅጥር ግቢ እየወሰዱ መጠቀም የተለመደ እንደነበርም እስከቅርብ ጊዜ እየታየ ያለ ነው። ለዚህም ብዙዎቻችን ዛሬ ድረስ ምስክር የምንሆንላቸው በአካባቢያችን ያሉ የእርሻ ልማት ጣቢያዎችን ልናነሳ እንችላለን።

ለምሳሌ፡- ደብረብርሃን ከተማ ላይ ያለው ረጅሙን ዓመታት ያስቆጠረው የመምህራን ኮሌጅ ለግቢው ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ ጭምር ብዙ አትክልትና ፍራፍሬን በዘመናዊ የእርሻ ጥበብ በቅናሽ ዋጋ ጥራት ያለው ምርት ዛሬ ድረስ ያቀርባል። ሻገር ስንል የሸዋሮቢት ማረሚያ ቤትም እንዲሁ ምርቶቹ የተለዩና በአገር ጭምር የሚታወቁ አድርጓቸው ቀጥሏል። ወደ ሁሉም አቅጣጫና ክልል ብንሄድ ብዙዎችን ዘርዝረን የማንጨርሳቸውን ማሰልጠኛዎች፣ የማህበረሰቡ መጋቢዎችን ማንሳት እንችላለን። ለዚህ ደግሞ መሰረቱ ምንም ሳይሆን የእርሻ ትምህርት ነው።

ትናንት ችግኝ ማፍላት አንዱ የትምህርት አካል ነበር፤ ችግኞችን መንከባከብም እንዲሁ። ይህ ሲሆን ደግሞ መደብ ጭምር ተሰጥቶ ነው። እናም ውጤቱ የሚለካው በአለው ውጤታማነት ልክ ነበር። በተጨማሪም የእንሰሳት ባህሪን መለየት፤ የቻሉትን ህክምና መስጠት፤ ቤተሰብን በግብርናው ዘርፍ ማገዝ የመሳሰሉ ነገሮችንም የእርሻ ትምህርት ካበረከታቸው ነገሮች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ከዚህ አኳያ ትምህርቱ ዳግመኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ተደርጎ ለተማሪዎች መሰጠት መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ነው። በእርግጥ የእርሻ ትምህርትና ተግባሩ በነበረበት ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ለአገራችን ብቻ ሳይሆን ለአለምም ጭምር እንተርፍ እንደነበር ማንም ይረደዋል። ከእነዚህ ዘመን ተሻጋሪ አምራቾች አንጻር አይተንም መገመት የምንችለው ይህንኑ ነው፡፡ዛሬም ይህው በጎ ተግባር እንዲቀጥል ትምህርት ሚኒስቴር በአዲሱ የትምህርት ስርዓት አካቶት ይዞት ብቅ ብሏል።

### ግብረገብነት

ይህ ትምህርት የተጀመረው ገና ዘመናዊ ትምህርት ወደአገራችን ከመግባቱ በፊት በቄስ ትምህርትቤት እንደሆነ ታሪክ ያስረዳል። እንደውም ዘመናዊው ትምህርት እንኳን ሲጀመር መምህራኑ ከዚያው የተውጣጡ እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ። እናም ያ ዘመን መምህራን የሚከበሩበት፤ ጎረቤት እንደ አባትና እናት የሚታይበት፣ ልጅ ከልጅ የማይለይበት፤ ታላቅ ለታናሹ የሚያዝንበት፤ታናሽ ታላቁን የሚያከብርበት ሁሉም ለሁሉም ሰው የሆነበት ነበር። መተሳሰብ የበረታበት፤ አብሮ መብላትና መጠጣት ልምድ የሆነበትም ነበር። ሽማግሌ የሚከበርበት፣ ወጣቱ ጎንበስ ብሎ የሚታዘዝበትና በሱስ ያልተጠመደበትም ነበር። ያ ዘመን ትምህርትም ቢሆን ተፋልሞ የሚገኝበት ነው። ማለትም ስነምግባር የሌለው ልጅ መቼም ውጤታማ የማይሆንበት ነበርና።

ያ ዘመን ለንባብም ሆነ ለትምህርት ልዩ ትኩረት ይሰጥበታል። ዛሬስ ካልን ነገሩ ተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ተቆጪ ያጣና በስነምግባር የተሞረደ ትውልድ የሚያፈራ የትምህርት ስርዓት አለመኖሩ ነው። በተጨማሪም ዘመን አመጣሽ በርካታ ነገሮች መኖራቸው ነው።

ወሬው ከቴክኖሎጂው ጋር ብቻ በመሆኑ ማህበራዊ ትስስሮች ሳይቀሩ እየቀሩ መጥተዋል። አሁን አሁንማ ጎን ለጎን ማውራትም እየቀረ ነው፡፡እና ግብረ ገብነት ርቆናል። ሆኖም በአዲሱ የትምህርት ስርዓት አንዱ ሆኖ መካተቱ ነባር ባህላችንን ከማቆየቱም በላይ ራስን፣ ቤተሰብንና አገር ወዳድ ትውልድን ለማፍራት ያስችላል። ምክንያቱም የስነምግባር መኖር የመጀመሪያው ጥቅም መዋደድን ማጎልበት ነው።

### አገር በቀል እውቀት

አገር በቀል እውቀትን መጀመሪያ ስናነሳ ብዙዎቻችን ትዝ የሚለን ነገር ባህላዊ መድሃኒቶቻችን ናቸው። ብዙዎችን ፈውሰው ለዛሬ አድርሰዋቸዋል። ዛሬም ቢሆን እየተጠቀምንላቸው ከበሽታችን የምንድንበት አጋጣሚ ቀላል እንዳልሆነ ሁላችንም የምንረዳው ጉዳይ ነው። ከፈዋሽነታቸው አኳያም ብዙ ጥናቶች እንደተደረጉባቸውና በህክምና ሰጪ ተቋማት ጭምር እንዲከፈቱ የሆኑበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም። በተጨማሪም አውሮፓውያን ጭምር በኢትዮጵያ ባህላዊ ዕውቀቶች ዙሪያ ትኩረት አድረገው ምርምር ሲያደርጉም ይታያሉ።

አገር በቀል እውቀት አንድ ትርጓሜ የለውም። ግን ብዙ ነገሩ ገንዘብም ሕይወትም የሚሆን ነው። ለአብነት መድሃኒቱን አነሳን እንጂ ባህሉ፣ ወጉ፣ አኗኗሩ፣ የአሰራር ጥበቡ ወዘተ ዘርዝረን የማንጨርሰው ነገር ነው። እናም ከትምህርት አንጻር መሰጠቱ በርካታ ጠቀሜታዎችን ከግለሰብ እስከ አገር ድረስ ያስገኛል። እንዴት ከተባለ እውቀቶችን በማውጣትና በመጠቀም ነው። ሁሉም በአካባቢው ያለውን ነባር እውቀት በማጋራት፣ እንዲተገበር በመስራትም ነው። የተለያዩ ዕሴቶችንም በማስተዋወቅ አንድነትንና አብሮነትን ያጎለብታል፡፡

### ሥነ ጥበብ

ሥነ ጥበብ ብዙ አይነት የሰው ልጅ ድርጊቶችን የሚያጠቃልል ዘርፍ ነው። እንዲታዩ ወይም እንዲሰሙ፣ እንዲወደዱ ወይም እንዲተገበሩ የምንፈልጋቸውን ነገሮች በጥበብ ኃይል በሙያው እንዲፈጸሙ የምናደርግበት ድርጊት ነው። እናም ይህ ዘርፍ በአይነት ጭምር ተከፍሎ እናገኘዋለን። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል ስዕል ፤ የሐውልት ሥራ፤ ስነ ሕንጻን የመሳሰሉ ነገሮች አቅፎ የምናገኘው ነው። ሌላውና ከዚህ ዘርፍ የሚመደበው ኪነት የምንለው ሲሆን፤ ብዙዎቻችን ከኪነጥበብ ጋር አገናኝተን የምንጠቀምበት ነገር ግን በባህሪው የተለየ የሆነው የስነጥበብ አይነት ነው። ማለትም ኪነት ማለት እንደ ጭፈራ፣ ሙዚቃ፣ ቴአትር፣ ፊልም፣ ስነጽሑፍን የሚይዘው ክፍል ነው።

ይህ የትምህርት አይነት በጥበብ ተመርቶ ራስን ማነጽ የሚያስችል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ይህ የትምህርት አይነት ሁሉም ትርጉም ያላቸው የጥበብ ሥራዎችን በመያዝ የሚያስፈልጉትን ፅንሰ-ሀሳቦችን ፣ የፈጠራ ችሎታን ፣ የእጅ ጥበብና የመሳሰሉትን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችልም ነው። ለሁሉም ተማሪዎች የሚያዳብሩበት ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ የበለፀገ እና የተከበረ አካባቢን ይሰጣቸዋልም። በተጨማሪም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሕዝቦች መካከል የመተማመንና የመግባባት ድልድይ ይገነባል፤ ከግለሰብ እስከ አገር ድረስ ያለውን ማንነትም ያጎላል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ትምህርቱ ውበት እና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን ያረካል።

የእውቀትን ፍላጎት ያሰፋል። ራስን ለመግለጽ ያለን ዝግጁነት ያዳብራል፤ ባህላችንን የምናስተዋውቅበትን እድል ይሰጣል። እናም በአዲሱ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተካቶ መምጣቱ ይበል የሚያሰኝ ነውና ከፖሊሲው ባሻገር አይተን እንጠቀምበት በማለት ተሰናበትን። ሰላም!!

# ወቅታዊ

# ‹‹ ሸኔ ከአሸባሪው የሕወሓት ድርጅት ጋር ስምምነት አድርጎ በጋራ መሥራቱ የባንዳ ባንዳ መሆኑን ያሳያል››

*አቶ ኢብሳ ነጋዎ*
*የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አማካሪ*

አስቴር ኤልያስ

**አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በመንግስት የተዘረጋለትን የሰላም እጅ አልቀበልም በማለት ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት መክፈቱ የሚታወቅ ነው። ህጻናትን በጦርነት በመማገድ፣ የእርዳታ እህልን የግዳጅ ማስፈጸሚያ(መያዣ) ማድረግ የተለመደ የጭካኔ ተግባሩ ሆኗል።በዚህም ድርጊቱ የእናቶችን እንባ የሚያፈስ፤ በእናቶች እንባ የሚደሰትና የሚረካ ቡድን መሆኑን አስመስክሯል። በስልጣን በቆየባቸው 27 ዓመታት ውስጥም ለዜጎች ስቃይ ትልቁን ሚና የተጫወተ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲያደርስ የነበረው ጫና የሚዘነጋ አለመሆኑ ይታወቃል። በሌላ በኩል አሸባሪው የሸኔ ቡድን ለኦሮሞ ሕዝብ ነጻነት የቆምኩ ነኝ ይበል እንጂ የኦሮሞን ሕዝብ ሲበድልና ጫና ሲፈጥርበት መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም። ይባስ ብሎ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ተጽዕኖ ሲያደርስ ከነበረው ከሕወሓት ቡድን ጋር በጥምረት እየሰራ ስለመሆኑ ይነገራልና በዚህ እና በሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር አማካሪ ከሆኑት ከአቶ ኢብሳ ነገዎ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሕወሓት የኦሮሚያን ሕዝብ ሲጨን፣ ተጽዕኖ ሲፈጥር፣ መብቱን ሲገፍ እንዲሁም ሀብቱን ሲዘርፉ የቆየ ነው፤ ከዚህ ቡድን ጋር የሸኔ አብሮነት መፍጠር ከሞራል አኳያ እንዴት ይታያል? ምክንያቱም የኦሮሞ አባቶች ከዚህ ድርጅት ጋር አብሮ መሰለፍ በራሱ ውርደት ነው ብለዋልና እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ኢብሳ፡-** በእርግጥ ከዚህ በላይ ውርደት የለም። በኦሮሞ መካከል እንኳን ሰው እርስ በእርሱ ቢገዳደል አንዱ የሌላውን ጎሳ በደንብ ስለሚያውቅ ችግሩ በጉማ ስርዓት ይፈታል። በአንድ ቀን ብቻ በብዙ መቶ የሚቆጠር ህዝብ የጨረሰ ቡድን ነው፤ ይህ ቡድን ወደዚህች አገር ከገባ በኋላ አገሪቱን ያላደረጋት ነገር የለም። ከኦሮሞ ሕዝብ ብቻ እንኳን የጠፋና የት እንደደረሰ ያልታወቀ ብዙ ሰው አለ። ሴቶች ተደፍረዋል፤ እናቶችን አሸማቋል። ነጋዴዎችን አደህይቷል። ሌላው ቀርቶ የአዲስ አበባ አካባቢን ብቻ መውሰድ ቢቻል የቱለማ አርሶ አደርን አፈናቅለው አስለቅቀዋል። ከዚህ ቡድን ማለትም መንግስትን ከስልጣን በማወረድ ተመልሰን ስልጣን እንይዛለን ከሚለው ጋር መሰለፍ በራሱ ውርደት ነው። ይህ ቡድን ሌላውን አካል የበታች አድርጎ ማስተዳደር የሚፈልግ ነው እንጂ በእኩልነት አብሮ ማደግን የሚፈልግ አለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው።

የፌዴራል ስርዓትን በአግባቡ ተከትለው እና ዴሞክራሲያዊ አድርገው መሄድ የሚፈልጉ ሳይሆን ስርዓቱን ለእነርሱ በሚመች መልኩ አዛብተው በመጠቀም ማስተዳደርን የተጠሙ ናቸው። ይህ አቋማቸውም በእነርሱ ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሮባቸዋል። ስለዚህም የገዳ አባቶች ይህ ውርደት ነው ያሉት ነገር ትክክል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሸኔ ከአሸባሪው ቡድን ጋር በተለያየ መንገድ የተሳሳኪነት ስራ እየሰራ ነው፤ ሀገር እያተራመሰ፣ ንጹሀንን እየገደለ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ከላዩ ላይ ያነሳውን አሸባሪውን ቡድን ዳግም ወደራሱ እንዲመለስ መስራቱን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ኢብሳ፡-** በአገራችን የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች የዚህ አሸባሪ ሕወሓትን ጉዳይ ጠንቅቀው የሚያውቁት ነው። አሸባሪው ሕወሓት በሐሰት ፕሮፓጋንዳ የቆመ ድርጅት መሆኑም ይታወቃል። ከሐሰተኛነቱ ባሻገር ደግሞ ሁሉም ሰው በየጊዜው ይሞኝልናል ብሎ የሚያስብ ድርጅት እንደሆነም በግልጽ እየታወቀ መጥቷል። ምክንያቱም ትናንት ሲናገር የነበረውን ጉዳይ ዛሬ ላይ አይደግመውም። ዛሬ የተናገረውን ነገር ደግሞ ነገ አይደግመውም። የሚቀባጥረው ሌላ ነገር ነው። ስለዚህም ተዓማኒነት የሌለው ቡድን ነው። ስለሆነም ከዚህ ድርጅት ጋር የሚሰራ አካል እርሱ የሚሰራውን ተከትሎ የሚሰራ ነው ማለት ይቻላል። የኦሮሞ ሕዝብ ግን ይህን ዋሾ ቡድን የሚከተለውን አካል (ሸኔን) ንቆታል። ከዚህ ቡድን ጋር የሚቆምን አካል ኦሮሞ ነው ብሎ ማለት ደግሞ አይቻልም። ይህ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ በአሁኑ ወቅት በአግባቡ እየታወቀ መጥቷል። ከዚህ ቀደም አንድ የኦሮሞ ሰው የሆነ ነገር ሲናገር በጅምላ ተወስዶ ከዚህ አካል ጋር አይይዞ የመታሰቡ ሁኔታ ነበር። ይህ ነገር ትልቅ ስህተት ነው። ኦሮሞ ታላቅ ሕዝብ ነው። አሁን ያለው መንግስት የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግስት ነው። የብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ ደግሞ እያስተዳደረ ያለው የኦሮሞ ልጅ ነው። ከወያኔ ጋር


ፎቶ - ከፋይል

**“ ባንዳ መሆን ሌላ ነገር ሲሆን ለባንዳ ደግሞ ባንዳ ሆኖ መስራት ሌላ ጉዳይ ነው።**

የሚቆመው ሸኔ ግን ለኦሮሞ ሕዝብ ግድ የሌለው መሆኑን የሚያመላክት ሆኖ ተገኝቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ሕወሓት ትናንትም ዛሬም እያደረገ ያለው ተግባር ግፍና ጭካኔ የተሞላበት ሆኖ ሳለ ሸኔ ከዚህ ቡድን ጋር መስራቱ እውን ለኦሮሞ ሕዝብ አስቦ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ኢብሳ፡-** በዚህ ጉዳይ በተደጋጋሚ ስናገር ቆይቻለሁ። ባንዳ መሆን ሌላ ነገር ሲሆን ለባንዳ ደግሞ ባንዳ ሆኖ መስራት ሌላ ጉዳይ ነው። የታላቁ ኦሮሞ ብሔር ታሪክ እንደሚያመለክተው ደግሞ አንዴም ቢሆን እንኳን ባንዳ ሆኖ የሚያውቅ አለመሆኑን ነው። የኦሮሞን ሕዝብ እየበደሉ ከሌላው ጋር እየሰሩ ያሉ አካላት ደግሞ እየሰሩ ያለው ጉዳይ የተለየ ነገር ነው። ወደፊትም ቢሆን የባንዳ ተላላኪ ሆነው እየሰሩ ያሉ እንደነዚህ አይነት ሰዎች ለራሳቸው የተዋረዱ እና ደካማ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

እንደሚታወቀው የሕወሓት አስተዳደር ከኦሮሞ ሕዝብ የበለጠ ተጽዕኖ የፈጠረበት ብሔር ያለ አይመስለኝም። በተለይ በግድያውም ቢሆን፣ የኦሮሞን መሬት በመቀራመትም ይሁን ትልቅ ጫና በማሳደሩ በኩል የተቻለውን ሁሉ ሲሰራ የነበረ ቡድን ነው። የኦሮሞን ባለሀብቶችም ሆነ ነጋዴዎችን በማደህየቱ በኩል የተቻለውን ሁሉ ያደረገ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኦሮሞ ምሁራንን ከአገር በማባረሩም በኩል የሰራው ስራ የማይረሳ ነው። በተለይ በተቻለው ሁሉ ምሁራኑን በማስፈራራት አገር ጥለው እንዲሰደዱ ማድረጉም ይታወቃል።

ይህ ከሆነ በኋላ የሕወሓት ግፍ የመረረው የኦሮሞ ሕዝብ ታግሎ ሕወሓት ወደ ክልሉ እንዲገባ ምክንያት ሆኗል። ይህን ግፍ ሲፈጽም የነበረውን ቡድን የኦሮሞ ሕዝብ አባርሮ ወደክልሉ ካስገባ በኋላ ይህን ቡድን መልሶ እንዲመጣ የሚሰራ አካል ቀድሞም ቢሆን ከዚህ ቡድን ጋር ትስስር ያለው በመሆኑ የኦሮሞን ሕዝብ የሚወክል አይሆንም። የኦሮሞ ሕዝብ ማንነቱን ተረድቶ የሚኖር ነው። አንድ አሸባሪ ቡድን ያጠፋው ጥፋት ትልቁን የኦሮሞ ሕዝብ የሚወከል አይሆንም።በአሁኑ ሰዓት በዚህ አካል ጥፋት ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ እንደማይወከልም ሕዝቡ እየተረዳ ይገኛል።

አሸባሪው ሕወሓት ሕዝብን እያሰቃየ እና ከብቱንም እየዘረፈ እንደሆነ ተረድተናል። ሌላው ቀርቶ እህል ያቃጥላል። ትምህርት ቤቶችን ያወድማል፤ ይህ አይነቱ አካሄድ ጥፋት ነው ብቻ ተብሎ የሚነገር ሳይሆን ቡድኑ እልህ ውስጥ የገባ አይነት ስራ እየሰራ በመሆኑ ወንጀሉ ከፍ ያለ ነው። ተላላኪው ሸኔም ከዚህ አይነት ጠላት ጋር አብሮ መስራቱ በኦሮሞ ላይ ያለውን ጠላትነት ከፍ ያደረገዋል። ስለሆነ የኦሮሞ ሕዝብ ይህን ተረድቶ ማንነቱን ለይቶ ተገንዝቧል።

እኔን ጨምሮ ሌሎቻችን በጉዳዩ ላይ በማማከር እንሰራለን። በጠብመንጃ አፈሙዝ ስልጣንን ማግኘት አይቻልም። ስልጣን ማግኘት የሚቻለው ሕዝብ ወድዶና ፈቅዶ ከመረጠው ከምርጫ ኮሮጆ ነው። ከዚህ ውጪ ያለው ግጭት ነው። ሰላም የማይኖር ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲ ይሉት ነገር አይኖርም። ወጥቶ መግባትም አይታሰብም።

በትግራይ ክልል ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ትልቅ ችግር መሆኑ የሚታወቅ ነው። ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ወጣት እያለቀ መሆኑ ይነገራል። እሱ ብቻ

# ወቅታዊ

አይደለም፤ በአማራ ወሎ አካባቢም ይኸው ቡድን ገብቶ ምን ሲያደርግ እንደነበር የሚታወቅ ነው። የተሰራውን ስራ ከማበላሸት እና ሕዝቡ በድህነት እንዲማቅቅ ከማድረግ ውጪ በጠብመንጃ አፈሙዝ የናፈቁትን ስልጣን መመለስ እንደሆነ የማይታሰብ ነው።

ስለዚህ ጦርነት መጥፎ ነገር ነው። ከዚህ ጦርነት ናፋቂ ከሆነው ቡድን ጋር የቆመው ሸኔ በኦሮሞ ሕዝብ ውስጥ ሆኖ እየኖረ ከባዕዳን ጋር ማበሩን የሚቀጥል ከሆነ ለቡድኑ ያው ተገዢ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ይህ አካል በምንም መስፈርት ኦሮሞን የሚወክል አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪዎቹ የሕወሓትና የሸኔ ጥምረት ግቡ የት ድረስ ነው? የሕወሓት ተቀዳሚ ዓላማ የሸኔም ጭምር ነው ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ኢብሳ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ የሸኔ ንቃተ ሕሊና አነስተኛ ነው። ይህን ያልኩበት ምክንያት አንደኛ የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ የአማራም ሕዝብ እንዲሁም ሌላውም ሕዝብ የወያኔን መንግስት ለዓመታት ሲታገሉት የነበረ ነው። ከዚህ ውስጥ ደግሞ በበለጠ ሁኔታ የተጎዳው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር እና የኦሮሞ ሕዝብ ነው። ይህ ሕዝብ ይበልጡኑ በወያኔ አስተዳደር የተጎዳ ስለነበር የኦሮሞ ወጣቶች ቄሮና ቀሬዎች እንዲሁም የአማራ ፋኖዎች በጥቅሉ በአገሪቱ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች ታግለው ወያኔን ከስልጣን ካስወገዱ በኋላ ተመልሰው ከእነርሱ ጋር መስማማት እና አብሮነትን መፍጠር ምን አይነት የፖለቲካ አካሄድ እንደሆነ ለእኔ አይገባኝም።

ቀደም ሲል ታስታውሱ እንደሆነ የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የኢሬቻ በዓል ላይ የተገኙ ወጣቶችን መግደሉም የማይረሳ ትዝታ ነው። ከዚህ በመግደልም በማሰቃየትም ታትሮ ከሚሰራውና አስከፊ ከሆነው ከወያኔ ድርጅት ጋር ሸኔ ስምምነት አድርጎ መስራቱ በእውነት ይህ ድርጊቱ የባንዳ ባንዳ መሆኑን ይገልጻል። አድራጎታቸው ትምህርት ቤት ማቃጠል፣ አስገድዶ መድፈር፣ ሕዝቡን መዝረፍ፣ የጤና ተቋማትን ማፍረስ ነው። ሌሎችን ብሔር ብሄረሰቦች ደግሞ ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር ለማጋጨት ብዙ ስራ ከመስራቱ ጎን ለጎን ንጹኃን ዜጎችንም የመግደሉ ሁኔታ በጣም አሳዛኝ ድርጊት ነው። ስለዚህ ግብ ወይም ርዕይ ያለው የፖለቲካ ድርጅት እንዲህ አይነቱን ተግባር አይፈጽምም።

**አዲስ ዘመን፡- ሕወሓትም ሆነ ሸኔ በሕዝባቸው ላይ እያደረሱት ያለው ድርጊት ከልክ ያለፈ ነው፤ ይህ የሚቀጥለው እስከ መቼ ድረስ ነው? ሸኔስ ቢሆን እስከምን ድረስ ነው ከሕወሓት ጋር በመሆን ዓላማውን የሚያራምዱት?**

**አቶ ኢብሳ፡-** ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት እስከፈቀዱ ድረስ በተላላኪነቱ ይቀጥላል ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም በዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ ወጣቶች እስከ ትግራይ ድረስ ሔደው እየተዋጉ ነው። በዚህም ደግሞ የቆሰሉ እና የተማረኩም አሉ። ጉዳዩ ሲገባቸው ሕዝባቸውን ይቅርታ ጠይቀው ይመለሳሉ የሚል እምነት ነው ያለኝ። አገሪቱን እያስተዳደረ ያለው መንግስት ለሁሉም የሰላም እጁን ዘርግቷል። በዚህ በተዘረጋው የሰላም እጅ ተቀብሎ መጠቀም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ።

በአጠቃላይ የሰው ልጅ ሰውን በመግደል ፖለቲካዊ ትርፍ ብሎም ኢኮኖሚያዊ ትርፍ ለማግኘት የሚያደርገው ሁኔታ በፈጣሪም ዘንድ ትልቅ ኃጢያት ነው ብዬ አምናለሁ። ይህን ሁኔታ በአግባቡ ተገንዝበው ከሕወሓት ቡድን ጋር ከመተባበር ይልቅ ቢለያዩ የሚል ጥሪ ማቅረብ እፈልጋለሁ። በሌሌላ መንገድ ደግሞ ንጹሃን ሰዎችን የመግደል ሁኔታ ከተጠያቂነት እንደማያስቀራቸው ከወዲሁ መገንዘቡ የተሻለ ነው የሚል አተያይ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የኦሮሞ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሸኔ እኩይ ተግባር ሊጠበቅ የሚችለው እንዴት ነው ብለው ያስባሉ፤ መፍትሔው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ ኢብሳ፡-** ወያኔ ከዚህ ቀደም በስልጣን በነበረበት ጊዜ 27 ዓመት ሙሉ ከእሱ የሚጠበቀውን አድርጓል። አሁንም ደግሞ ከስልጣን በትብብር እንዲነሳ የተደረገ ቢሆንም በራሱ ሕዝብ ላይ ደግሞ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየሰራ ነው ብዬ አምናለሁ። ለምን ቢባል የአንድ አገር ወይም የአንድ ብሔር ወጣቶች በጅምላ አስጨፍጭፎ በግድ ወደጦርነት እንዲገቡ በማድረግ እና እንዳይመለሱም ከኋላ በመሆን ለጦርነት ማግዷቸዋል። በዚህም ወጣቱን አስጨፍጭፏል ማለት ይቻላል። ምን ያህል የትግራይ ወጣቶች እንዳለቁ ወደፊት በጥናት የሚገለጽ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እስካሁን ግን በግምት ወደ 800 ሺ እና ከዚያም በላይ እንደሆነ ነው እየተነገረ ያለው። ታድያ ይህ ሁሉ የትግራይ ወጣት የሚያልቅ ከሆነ ጦርነቱስ ለማን ነው፤ ያረጁ እና ያፈጁ የሕወሓት አመራሮች ለማን ነው የሚቆሙት? የሚታገሉትስ? ከዚህስ በኋላ የሚጠብቁት ምንድን ነው? በአገሪቱ የስልጣን ርካብ ላይ በነበሩበት ወቅት 27 ዓመት ሙሉ ሕዝብን ሲበድሉ የቆዩ ናቸው። እንደገና ደግሞ እንታገላለን ወደሚሉለት ሕዝብ መጥተውም እንዲሁ ሲጨቁኑ ከርመዋል። ከዚህም አልፈው ሕዝቡን አስጨርሰዋል። ይህም ራሱን የቻለ የተለየ ወንጀል ነው።



እነዚህ አካላት አገሪቱንም አስተዳድራለሁ ያሉትንም ሕዝብ ሲበዘብዙና ሲያሰቃዩ ኖሩ እንጂ እነርሱ ግን የችግሩ ገፈት ቀማሽ አልነበሩም። በአንጻሩ እነርሱ ቢሊየነሮች ናቸው። ትልልቅ አፓርታማዎች ያሏቸው ናቸው። ታድያ ስለምንድን ነው ግፍ እየፈጸሙ ያሉት ተብሎ ቢጠየቅ መልሱን የሚያውቁት እነርሱ ብቻ ናቸው። በእኛ እይታ ግን ሕዝባቸውን እያስጨረሱ ስለሆነ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረጉ ተገቢ ነው ብለን ነው የምናስበው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሕወሓት እና ከሸኔ ጋር በተያያዘ የኦሮሞ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቁ እንዲሆን ምን ማድረግ ይገባቸዋል ይላሉ?**

**አቶ ኢብሳ፡-** በአጠቃላይ ማለት የምፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ደግሞ የኦሮሞና የአማራን ሕዝብ በእነዚህ አካላት እየተደረገ ስላለው እንቅስቃሴ አስተዋዮች ሆነው ሊያዩ ይገባል ነው። በተለይ በእነዚህ አካላት ጠንሳሽነት የኦሮሞ እና የአማራ ሕዝብ እንዲጋጩ ያልተደረገ ጥረት የለም ለማለት ይቻላል ። አንዱን በሌላው ላይ በማነሳሳት በጠላትነት እንዲፈረጁ ያልተደረገ ሙከራ የለም። በኦሮሚያ ክልል መለስ ብለን የበደኖን እና ሌሎችንም ብናስታውሳቸው የተቀነባበረው በሕወሓት እንደነበር ይታወሳል። ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ጭካኔ የተሞላበትን አካሄድ ወደ ጎን በመጣል እርስ በእርስ አንድነትን ፈጥሮ መንቀሳቀሱ ከምንም በላይ ተመራጭ መሆኑን መረዳት መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፈው ሰሞን ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የባለሙያዎች ቡድን በኢትዮጵያ ላይ አካሂጄዋለሁ ያለው ‹‹ሪፖርት›› ይፋ መደረጉ ይታወቃል፤ ይህ በመንግስት በኩል ተቀባይነት ያጣው ‹‹ሪፖርት›› እውን ለሰብዓዊ መብት ከመቆርቆር የተነሳ የተሰናዳ ነው ብለው ያስባሉ።**

**አቶ ኢብሳ፡-** በዚህ አካል ተጠንቶ የቀረበው ሪፖርት አነሳሱ ራሱ የፖለቲካ ቅኝት ያለው ነው። በመጀመሪያ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚያሳይ ጥናት ለመሆኑ ሕጋዊና ሙያዊ ሊሆን ይገባው ነበር፤ ነገር ግን ይህን ሳይንሳዊ አካሄድ የተከተለ አይደለም። በእርዳታ ስም፣ በሰብአዊ መብት ስም የሚደረግ አካሄድና በመንግስት ላይ ጫና ለማሳደር የታሰበ ሴራ ነው። በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አካላት በስልክ አነጋግሮ እንደዛ አይነት ሪፖርት ይፋ ማድረግ በእርግጥም የሚያስቅም የሚያስገርምም ነው። ለምን ቢባል በአፋር፣ በአማራ የተገደሉ የየክልሉ ሕዝቦች፣ የተደፈሩ ሴቶች፣ የተቃጠሉ መሰረተ ልማቶች ከግምት ውስጥ የገቡ አይደሉም፤ ሌላው ቀርቶ በባለፈው ጊዜ በጋሊኮማ ብቻ የደረሰው አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ግፍ ብቻ በቂ ነበር። ስለሆነም ይህ አይነቱ አሰራር ሆን ተብሎ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና ለማሳደር ሲባል የተደረገ እንጂ በእርግጥ ለሰብዓዊ መብት ተቆርቁረው ያጠኑት እንዳልሆነ ነው የሚገባኝ። በመሆኑም ምርመራቸው ትክክለኛ አይደለም ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከትናንት በስቲያ በአዲስ አበባ፣ ትናንት ደግሞ በቢሾፍቱ የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን የሚያቀርብበት የኢሬቻ በዓል መከበሩ ይታወቃል፤ የዚህ በዓል ትሩፋቱ ምንድን ነው ይላሉ?አንዳንዶች ፖለቲካዊ ነው ሲሉ ይደመጣል።**

**አቶ ኢብሳ፡-** ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የሚከበር በዓል ነው። ይህን በዓል የተለያየ እምነት ያላቸው ሁሉ የሚያከብሩት ነው። ምክንያቱም የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው ለአምላክ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል በመሆኑ ነው። ኢሬቻ ፖለቲካ አይደለም።

ይህ የኢሬቻ በዓል በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ለብዙ መቶ ዓመታት ሲከበር የነበረ ነው። ኢሬቻ የሰላም የእርቅና የተጣላ ሁሉ ሰላም የሚፈጥርበት የአንድነት በዓል ከመሆኑም በተጨማሪ ለወደፊትም ቢሆን የሰላም፣ የእድገት እና የሰው ልጅ ወንድማማችነት የሚገለጽበት በዓል ነው። ብሎም እግዚአብሔር የሚመሰገንበት እንዲሁም መጥፎ ስራዎች ደግሞ እንዳይደገሙ የሚደረግበትም ጭምር ነው። በዓሉ በተለይ ሰዎች በአንድነት ይበልጥ እንዲያከብሩት የሚደረግበትም ነው። ኢሬቻ በአያያዙ ከገዳ ስርዓትም ጋር የሚሄድ ነው። የገዳ ስርዓት እንደሚታወቀው የእኩልነት ስርዓት ጎልቶ የሚታይበት ስለሆነ ኢሬቻም የእሱ ነጸብራቅ ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ብቻ እንዳይሆንና ሌሎችንም ከማካተቱ አኳያ አቃፊነቱስ የት ድረስ መሆን አለበት ይላሉ?**

**አቶ ኢብሳ፡-** እንደሚታወቀው የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ጋር አብሮ መሆኑን ማሳያ የሚሆኑ በርካታ ባህልም ትስስርም ያለው ነው። ለምሳሌ ማንሳት ካስፈለገ የኦሮሞ ባህል በጉዲፈቻም ከሌሎች ጋር አንድነቱን የሚፈጥርበት ነው። የኦሮሞ ሕዝብ በዘመኑ በጦርነት ላይ የተማረከውንም የራሱ ጎሳ አድርጎ እንዲሁም ልጁን ሰጥቶ ከሌሎቹ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በሰላም የሚኖር ሕዝብ እንደነበርም የሚታወቅ ነው። አሁንም ቢሆን ያንን ሁኔታ በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር እንዲተረጎም ነው በሕዝቡ ዘንድ የሚፈለገው። ስለዚህም ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችን ማቀፉ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ እንግዳ አይደለም ለማለት ነው።

ለወደፊቱም ቢሆን በኢትዮጵያም ሆነ በምስራቅ አፍሪካ ያሉ ሕዝቦች በሰላም ተከባብረው አብረው እንዲኖሩ እና ከፖለቲካ እይታም ውጪ የአብሮነቱ ሁኔታ ፈጣሪ የሰጣቸውን የጎረቤትነትና የአብሮነትን ጉዳይ አጠንክረው የሚሄዱበት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ይህ የዘመኑ ጫፍ ረገጥ ፖለቲካ ደግሞ ፖለቲካኞች እውቅና ለማግኘት የሚደረገውን ሁኔታ እየለዘበ እንዲሄድ ሊያደርግ የሚችልም በዓል በመሆኑ ይህን የማጎልበትና በይዘቱም ወደአንድነቱ የመመለስ ስራ የሚሰራበት እንደሚሆንም አስባለሁ።

ቀደም ሲል የራስን ብቻ አተልቆና የሌሎችን የመግፋት አሊያ የመጥላት ወይም ደግሞ የማግለል ሁኔታ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ያልነበረ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ባህሉን የማክበሩ ሁኔታ ለኦሮሞ ሕዝብ ለራሱ እና ለሌሎችም ብሔር ብሔረሰቦች የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም። ሕዝቦች ተከባብረው እና ተዋድደው አብረው እንዲኖሩ የሚያግዝ ነው። ኢሬቻ ይህንኑ የሕዝቦች አንድነት የሚያስቀጥል ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ የኢሬቻ በዓል ማክበሩ ያለውን እሴት እና ባህል የሚያጎላበት እንጂ ሌሎችን የሚያገልበት ባለመሆኑ አቃፊነቱ ሰፊ ነው። በዓሉ አብሮነትም የሚጎላበት ነው። ይህ አብሮነት እንዲቀጥል ነው የሚፈለገው እንጂ ኦሮሞ የራሴ በዓል ነው የሚልበት ነገር የለውም። ወደድንም ጠላንም የዚህቹን አገር ሕዝብ እግዚአብሔር የፈጠረን አብሮ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ውጪ ሌላ አገር የለውም። ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ የመኖሩን ሂደት ያስቀጥለዋል እንጂ ከወንድሙና ከእህቱ ጋር ንትርክን አይፈጥርም። የኢሬቻ በዓል ትልቅ የሆነ የአንድነት ጥግን ዓላማው ያደረገ በዓል ይሆናል እንጂ የራስን በዓል ብቻ የማክበር እና ሌላውን የሚገፋ መሆን የለበትም። ይህ ሌላውን አሳንሶ የማየቱ ሁኔታ አስፈላጊም ተገቢም አይደልም፤ አይሆንምም። ደግሞም የመከባበሩ ሁኔታ የሚያሳጣው አንድነትን ነው፤ ስለዚህ በመከባበር ጥላቻንና መለያየትን ማራቅ ይቻላል።

ደግሞም እንለያይ ቢባል እንኳ የሚቻል አይደለም። ለምሳሌ የባል እና የሚስትን ሁኔታ ብትወስዷ ተስማምተው አብረው የመኖር ሁኔታ ላፈሯቸው ልጆች የበለጠ ጥቅም ያለው እንጂ የሚጎዳው አይደለም። ያለመስማማታቸው ግን ጉዳቱ ከራሳቸው አልፎ ለልጆቻቸው የሚተርፍ ነው። ይህ ደግሞ ከተጠያቂነትም አያስመልጣቸውም። ስለዚህ የመቻቻሉ ሁኔታ ከዚህ አኳያ መታየት አለበት ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡኝ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ኢብሳ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የያዙት የቡርኪናፋሶ መሪ መፈንቅለ መንግሥት ተደረገባቸው

የቡርኪናፋሶ የጦር መኮንኖች በብሔራዊው ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው የአገሪቱ ወታደራዊ መሪ ሌተናል ኮሎኔል ፖል ሄንሪ ዳምቢባ ከሥልጣን መወገዳቸውን አስታወቁ። የቡድኑ መሪ ሻምበል ኢብራሂም ትራኦሬ እንደተናገሩት፤ የወታደራዊ መሪው ሌተናል ኮሎኔል ዳምቢባ ከመሪነት የተወገዱት በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱትን እስላማዊ አማጺያንን በአግባቡ መቆጣጠር አልቻሉም በሚል ነው።

መኮንኑ ጨምረውም ላልተወሰነ ጊዜ ሁሉም የአገሪቱ ድንበሮች ዝግ እንደሚሆኑ እና የትኛውም አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መከልከሉን አሳውቀዋል። አሁን ከሥልጣን መወገዳቸው የተገለጸው ዳምቢባ የሚመሩት ቡድን፣ ባለፈው ዓመት ጥር ላይ ነበር በሕዝብ የተመረጠውን አስተዳደር በመፈንቅለ መንግሥት ገልብጦ ወደ ሥልጣን የመጣው።

በወቅቱም ወታደራዊ ቡድኑ መንግሥት የእስላማዊ ቡድኖችን ጥቃት ማስቆም አልቻለም በሚል ነበር መፈንቅለ መንግሥት ማድረጉን ያሳወቀው። አርብ ጠዋት ላይ በዋና ከተማዋ ዋጋዱጉ ውስጥ ከባድ ተኩስ ከተሰማ በኋላ ሕዝቡ እንዲረጋጋ ሌተናል ኮሎኔል ዳምቢባ ጠይቀው ነበር። ምሽት ላይ ከ20 በላይ የሚሆኑ አብዛኞቹ ፊታቸው የተሸፈነ የታጠቁ ወታደሮች በብሔራዊው ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው የቡድኑ መሪ ናቸው በተባሉት ትራኦሬ የተፈረመ መግለጫ አቅርበዋል።

"እየተባባሰ የሚሄድ ችግር በገጠመን ጊዜ ዳምቢባ በደኅንነት ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ በተደጋጋሚ ሞክረናል፤ ነገር ግን የዳምቢባ ተግባር ለማድረግ ካቀድነው ውጪ በመሆኑ አሁን ከሥልጣን



እንዲወገድ ወስነናል" ብሏል መግለጫው። ከዚህ በኋላም በመላዋ አገሪቱ ከምሽት 3 ሰዓት እስከ ንጋት 11 የሚቆይ የሰዓት እላፊ ገደብ የተጣለ ሲሆን፣ ሌተናል ኮሎኔል ዳምቢባ የት እንዳሉ የታወቀ ነገር የለም።

አሜሪካ ቡርኪናፋሶ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ነገር "በእጅጉ እንዳሳሰባት" በመግለጽ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ዜጎቿ እንቅስቃሴያቸውን እንዲቆጥቡ መክራለች። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ቃል አቀባይ "መረጋጋት እንዲሰፍንና ሁሉም ወገኖች ከየትኛውም ድርጊት እንዲቆጠቡ" ጥሪ አቅርበዋል።

የምዕራብ አፍሪካ አገራት የኢኮኖሚ ማኅበር የሆነው ኤኮዋስ "ሥልጣንን ሕገ መንግሥታዊ ከሆነ መንገድ ውጪ መያዝና በሥልጣን ላይ መቆየትን አጥብቄ እቃወማለሁ" በማለት በቡርኪናፋሶ የተካሄደውን የመንግሥት ግልበጣውን አውግዞታል። አርብ ዕለት አጥቢያ በፕሬዚዳንቱ ቤተ መንግሥት እና በዋና ከተማዋ ዋጋዱጉ ውስጥ ባለ ጦር ሰፈር አቅራቢያ የተኩስ ድምጽና ፍንዳታ መጀመሪያ ላይ ተሰምቶ ነበር።

ይህንንም ተከትሎ ጠዋት ላይ ወታደሮች አንዳንድ መንገዶችን በመዝጋት ቁልፍ የከተማ ክፍሎች ላይ በመሰማራታቸው ለወትሮ ግርግር የሚበዛበት ከተማ ጭር ብሎ ነበር። ቀን ላይ የተኩስ ድምጽ የተሰማ ሲሆን የአገሪቱ ቴሌቪዥን ጣቢያም ስርጭቱን ለሰዓታት አቋርጦ ቆይቶ ነበር።

የመፈንቅለ መንግሥት ወሬ በስፋት በተናፈሰበት አርብ ከሰዓት በኋላ ፕሬዚዳንቱ ሌ/ኮሎኔል ዳምቢባ፣ በአንዳንድ ወታደሮች ዘንድ የተፈጠረ ስሜታዊነት "ግራ መጋባትን" መፍጠሩን በመግለጽ "ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ድርድር እየተካሄደ ነው" በማለት ሕዝቡ እንዲረጋጋ ጠይቀው ነበር።

አሁን ከሥልጣን መባረራቸው የተነገረው ዳምቢባ ባለፈው ዓመት ጥር ፕሬዚዳንት ሮች ካቦሬን እየጨመረ የመጣውን የእስላማዊ ታጣቂዎች ጥቃትን መቆጣጠር አልቻሉም በሚል ነበር በመፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣን ያስወገዱት። ነገር ግን ዳምቢባ ወደ ሥልጣን ከመጡም በኋላ በርካታ ዜጎች ደኅንነት እንደማይሰማቸው በመግለጽ በዚህ ሳምንት በተለያዩ የቡርኪናፋሶ ክፍሎች የተቃውሞ ሰልፎች ተካሂደዋል።

አርብ ከሰዓት በኋላ አንዳንዶች በዋና ከተማዋ ዋጋዱጉ ውስጥ ሌተናል ኮሎኔል ዳምቢባ ከሥልጣን እንዲወርዱ የሚጠይቅ ተቃውሞ ሲያሰሙ ነበር። በቡርኪናፋሶ የእስላማዊ ታጣቂዎች እንቅስቃሴ ከሰባት ዓመት በፊት የጀመረ ሲሆን፤ በዚህም ሳቢያ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ፣ ሁለት ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች ደግሞ ከቤታቸው ለመፈናቀል ተገደዋል።

ቡርኪናፋሶ በአውሮፓውያኑ 1960 ነጻ አገር ከሆነች በኋላ እስካሁን ድረስ ስምንት የተሳኩ መፈንቅለ መንግሥቶች ተካሂዶባታል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## በድጋሚየወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ መለያ ቁጥር CC-SB/CNB/01/2015/2022

በጉምሩክ ኮሚሽን የሰመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ለ2015 በጀት ዓመት ለሰመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤቱ እና ለመቆ/ጣቢያዎች እንዲሁም የቅ/ጽ/ቤቱ አመራሮች ለስራ አገልግሎት ለመገልገል 01/አንድ/ ሃይሉክስ ደብል (Double) ጋቢና ተሽከርካሪ በግልጽ ጨረታ ግዥ አወዳድሮ ለአንድ (01) ዓመት የሚቆይ ውል መያዝ ይፈልጋል በሰንጠረዡ በተቀመጠ ሃሳብ መሰረት አሸናፊ የሚሆን ድርጅት ውል መዋዋል ይፈልጋል።

| ተ/ቁ | የተሽከርካሪ አይነት | ሰው የመጫን | ስሪት ዘመን | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሃይሉክስ ደብል (Double) ጋቢና (ፒካፕ) | | 2002 እና ከዛ በላይ | 01 | የተሽከርካሪ ወንበር ጥራቱን እና ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ AC ያለው |

**ስለሆነም ተሽከርካሪዎችን የሚያመለክተው የጨረታው ዝርዝር ሁኔታ በጨረታው ሠነዱ ላይ መመልከት ትችላላችሁ።**

በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡


1. ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ።
2- ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ በግብር አስገቢው ባለስልጣን የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
3. ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።
4. የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ለሃይሉክስ ደብል (Double) ጋቢና በባንክ የተመሰከረለት C.P.O ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ከጨረታ ሠነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ።
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ብር) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰመራ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የግዥና ፋይናንስ ቡድን ቢሮ ህንፃ አንደኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባትይኖርባችዋል።
7. ጨረታው መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም ለተከታታይ ለ15 የስራ ቀን የሚቆይ ይሆናል።
8. ጨረታው ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4:30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
9. የጨረታው አሸናፊ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና 10% (አስር በመቶ) C.P.O በማስያዝ ከመስሪያቤቱ ጋር ውል ይፈራረማል።
10. ጨረታውን የምናስተናግደው በእያንዳንዱ ተሽከርካሪ (car by car) ይሆናል።
11. ተጫራቾች ከጨረታው ስነድ ላይ ስርዝ ድልዝ ሊኖረው አይገባም ካለውም ፓራፍ መደረግ አለበት።
12. ተጫራቾች ከሚሞሉት ሰነድና ፖስታ ላይ የድርጅታቸው ማህተም እንዲሁም ስም፣ አድራሻ ስልክ፣ ኢሜይል አድራሻ ማድረግ አለባችሁ።
13. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መኪናዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።
14. ተጫራቾች ተመሣሣይ የሰርቪስ ዋጋ ቢያቀርቡ ቃለ ጉባኤ በመያዝ በእጣ የምንለይ መሆኑንእናሳውቃለን ዘግይቶ የመጣ ተጫራች ፖስታ ተቀባይነት የለውም።
15. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ ሙብቱ የተጠበቀ ነው።

የጨረታ ሰነድ መሸጫና ጨረታ መክፈቻ ቦታ በሰመራ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት ግዥና ፋይናንስ ቡድን አስተባባሪ 1ኛ ፎቅ

**ስልክ ቁጥር: 03-33-66-88-39/03-33-66-15-67/ 03-33-66-31-27/09-26-63-21-23**

**ኢ.ፌ.ዴ.ሪ የጉምሩክ ኮሚሽን ሰመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት



# ያለምዘርፍ የኋላው የለንደን ማራቶንን በድንቅ ብቃት አሸነፈች

**ቦጋለ አበበ**

በየአመቱ በተለያዩ የአለማችን ከተሞች ከሚካሄዱ ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች ግንባር ቀደም በሆነው የለንደን ማራቶን ኢትዮጵያዊቷ ወጣት አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ጣፋጭ ድል ተቀዳጅታለች። በደመናማና ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ታጅቦ ትናንት ውድድሩ ሲካሄድ ያለምዘርፍ በአስደናቂ ብቃት ተፎካካሪዎቿን በፍጹም የበላይነት መርታት ችላለች።

በውድድሩ ሰላሳ ሁለተኛ ኪሎ ሜትር አካባቢ ከተፎካካሪዎቿ ጋር ባደረገችው ትግል ወድቃ የተነሳችው ያለምዘርፍ ተስፋ ባለመቁረጥ ወደ አሸናፊነት የመጣችበት ሁኔታ አስደናቂ ነበር። የሃያ ሶስት አመቷ ድንቅ ኢትዮጵያዊት አትሌት በመጨረሻው አምስት ኪሎ ሜትር ፍጥነቷን ጨምራ በመሮጥ በተፎካካሪዎቿ ላይ የወሰደችው የበላይነት በ2:17:26 ሰአት የድሉ ባለቤት ለመሆን አስችሏታል። በዚህም የለንደንን ማራቶን በትንሽ እድሜ ያሸነፈች የመጀመሪያ አትሌት ለመሆን በቅታለች።

ያለምዘርፍ በተለይም ያለፈው ውድድር አሸናፊና ትልቅ ግምት የተሰጣትን ኬንያዊቷን አትሌት ጆይስሊን ጄፕኮስጌን በመጨረሻው አምስት ኪሎ ሜትር ፋታ በማይሰጥ ፍጥነትና ጥንካሬ ማንበርከኳ አድናቆትን አትርፎላታል። ያስመዘገበችው ሰአትም ቀደም ሲል በርቀቱ ካስመዘገበችው የኢትዮጵያ ክብረወሰን በሶስት ሰከንድ ብቻ የዘገየ ሆኗል። ባለፈው ሳምንት የበርሊን ማራቶን አትሌት ትእግስት አሰፋ አሸናፊ ስትሆን፤ የኢትዮጵያን የማራቶን ክብረወሰን መስበሯ የሚታወስ ሲሆን ከዚያ ቀደም ክብረወሰኑ በያለምዘርፍ እጅ ነበር የሚገኘው።



አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ሁለት የማራቶን ውድድር አድርጋ ሁለቱንም በድል ፈጽማለች፣

ያለምዘርፍ ለዚህ ታላቅ ድል የበቃችው ገና በሁለተኛ የማራቶን ውድድሯ ነው። በሁለቱም ውድድሯ ግን አርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩን ያጠናቀቀችው 2:17 ቤት ነው። ይህች ድንቅ አትሌት በግማሽ ማራቶን ውድድርም በታሪክ ሁለተኛዋ ፈጣን አትሌት ስትሆን የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር ክብረወሰንም በእጇ ይገኛል። ባለፈው ሚያዝያ በሃምቡርግ የኢትዮጵያን የማራቶን ክብረወሰን ስትሰብር ያስመዘገበችው 2:17:23 በርቀቱ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሮጠች አትሌት የተመዘገበ ፈጣኑ ሰአት እንደነበር ይታወሳል። ይህም የአለማችን ሰባተኛው የማራቶን ፈጣን ሰአት ባለቤት ያደርጋታል።

ያለምዘርፍ ካስደናቂው የለንደን ማራቶን ድሏ በኋላ "በለንደን ማራቶን በማሸነፌ ተደስቻለሁ፣ ለዚህ ውድድር ጠንክሬ ስሰራና በጥሩ ሁኔታ ስዘጋጅ ቆይቻለሁ፣ ድሉም አስደናቂ ነው" በማለት ለመገናኛ ብዙኃን አስተያየቷን ሰጥታለች።

ከውድድሩ ቀደም ብሎ ብዙ የተነገረላት ያለፈው ለንደን ማራቶን አሸናፊዋ ጄፕኮስጌ ከባለድሏ አትሌት ከአንድ ደቂቃ ባላነሰ ዘግይታ በ2:18:07 ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። ልላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት መገርቱ አለሙ በ2:18:32 ሶስተኛ ሆና ጨርሳለች።

በተመሳሳይ በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ትልቅ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም በ2:05:53 ሰአት አምስተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል።

የመምና አገር አቋራጭ ውድድሮች ንጉስ የሆነው ቀነኒሳ ፊቱን ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች ካዞረ በኋላ በ2016 የለንደን ማራቶን ሶስተኛ፣ በ2017 ደግሞ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ የሚታወስ ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ከሚገጥመው ጉዳት ጋር እየታገለ በመምና በአገር አቋራጭ ውድድሮች የሰራውን ታሪክ በማራቶን ለመድገም ጥረት አድርጓል። በዚህም በ2019 የበርሊን ማራቶን በወቅቱ የአለም ክብረወሰን ከነበረው የኬንያዊው አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ በሁለት ሰከንድ የዘገየ 2:01:41 ሰአት በማስመዝገብ ማሸነፉ ይታወሳል። ቀነኒሳ ይህን አስደናቂ ብቃት ካሳየ በኋላ በርካቶች የርቀቱን የአለም ክብረወሰን እንደሚሰብር ተስፋ ቢያደርጉም አልተሳካለትም። ይህ የ40 አመት የምንጊዜም ድንቅ አትሌት በተለይም በ2020 የለንደን ማራቶን ክብረወሰን ያስመዘግባል ተብሎ ሲጠበቅ በመጨረሻ ሰአት በጉዳት ምክንያት ሳይወዳደር ቀርቷል። ከዚያ በኋላም በ2021 የኒውዮርክ ማራቶን ስድስተኛ ሆኖ ነበር ያጠናቀቀው። ቀነኒሳ ከሶስት ሳምንታት በፊት ወደ ውድድር ተመልሶ በእንግሊዝ ግሬት ኖርዝ ረን ባደረገው የ21 ኪሎ ሜትር ውድድርም ዩጋንዳዊው ጃኮብ ኪፕሊሞንና የቶኪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮኑን ሰለሞን ባረጋን ተከትሎ ሶስተኛ ሆኖ ማጠናቀቅ ችሏል።

ኬንያዊው አትሌት አሞስ ኪፕሩቶ በ2:04:39 አሸናፊ በሆነበት በትናንቱ የለንደን ማራቶን ኢትዮጵያዊው አትሌት ልኡል ገብረስላሴ በ2:05:12 ሰአት ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል። ቤልጂየማዊው አትሌት በሺር አብዲ በሶስት ማይክሮ ሰከንዶች ተቀድሞ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ፈጽሟል። ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናሉ ተብለው ሲጠበቁ የነበሩት ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ክንዴ አጥናው 2:05:27 አራተኛ፣ ብርሃኑ ለገሰ 2:06:11 ስድስተኛና ሲሳይ ለማ በ2:07:26 ሰባተኛ ደረጃን ይዘው አጠናቀዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 01/2015

የአየር አምባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ፋ/ግ/ን/አስ/የስራ ሂደት በጨረታ ቁጥር አየ/አ/2ኛ/ደረጃ ት/ቤት 01/2015 መሰረት የ2015 በጀት ዓመት ለመማር ማስተማሩ የሚውሉ እቃዎችን በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**የጨረታ ግዢ መለያ ቁጥር አየ/አ/2ኛ/ደረጃ ት/ቤት 01/2015**

| ተ.ቁ | የእቃውና አገልግሎቱ አይነት | የግዥ ሎት ምድብ | የግዥው ምድብ | የጨረታው ማስከበሪያ የብር መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የአላቂ የጽህፈት መሳሪያዎች | ሎት 1 | እቃ | 5000 | 00 |
| 2. | የደንብ ልብስ | ሎት 2 | እቃ | 5000 | 00 |
| 3. | የፅዳት እቃዎች | ሎት 3 | እቃ | 5000 | 00 |
| 4. | የፈርኒቸር እቃዎች | ሎት 4 | እቃ | 5000 | 00 |
| 5. | የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች | ሎት 5 | እቃ | 5000 | 00 |
| 6. | የህንፃ መሳሪያ እቃዎች | ሎት 6 | እቃ | 4000 | 00 |
| 7. | የስፖርት እቃዎች | ሎት 7 | እቃ | 4000 | 00 |
| 8. | ህትመት | ሎት 8 | አገልግሎት | 2000 | 00 |
| 9. | የደንብ ልብስ ስፌት | ሎት 9 | አገልግሎት | 2000 | 00 |
| 10. | የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥገና | ሎት 10 | አገልግሎት | 2000 | 00 |
| 11. | የኤሌክትሪክ መስመር ጥገና | ሎት 11 | አገልግሎት | 2000 | 00 |
| 12. | የፍሳሽ ማስወገድ/ሽንት ቤት ማስመጠጥ/ | ሎት 12 | አገልግሎት | 2000 | 00 |
| 13. | የውሃ መስመሮች ጥገና | ሎት 13 | አገልግሎት | 2000 | 00 |

* ከሎት ቁጥር 8 - 13 የተጠቀሱት የአገልግሎት ግዢዎች በበጀት ዓመቱ አገልግሎቱ በሚፈለግበት ወቅት በሚታዘዘው መጠን ልክ ሲሆን ውሉ ጸንቶ የሚቆየው እስከ በጀት አመቱ መዝጊያ መሆኑን እናሳውቃለን::

1. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፤ የዘመኑን ግብር የከፈለበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር ባዘጋጀው የእቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገቡ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል እና በ2015ዓ.ም በጨረታ መሳተፍ የሚችሉ መሆናቸው ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ አካል የተሰጣቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለበት፡፡
2. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን የጨረታውን ዝርዝር ሰነድ ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ ብር 100.00 / አንድ መቶ ብር/ በመክፈል መግዛት አለባቸው።
3. ከአቅራቢዎች ስም ዝርዝር ውስጥ በተለያዩ ጥፋቶች ያልተሰረዙ ወይም የቅጣት ጊዜያቸው ያልተጠናቀቀ በዚህ ጨረታ ላይ መሳተፍ አይችሉም፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) ለሚወዳደሩበት እቃ ከላይ በየሎቱ በተቀመጠው መሰረት በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ CPO ከጨረታው ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
5. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነድ ለማስገባት በሚመጣበት ጊዜ ሳምፕል ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች አብሮ ማስገባት አለበት ሳምፕል ለማቅረብ ምቹ ያልሆኑ እቃዎችን በፎቶ ማቅረብ ግዴታ ሲሆን ሳምፕል ያላቀረበ ተጫራች የጨረታውን ሰነድ የማናወዳድር መሆኑን በቅድሚያ ት/ቤቱ ይገልጻል።
6. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ዋናውን እንዲሁም CPO ከኮፒው ሰነድ ጋር በታሸገ ኢንቨሎፕ የድርጅቱን ማህተም በማድረግ እና በፊርማ በማረጋገጥ ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት ከጠዋቱ 2:30--11:00 ሰዓት በቢሮ ቁጥር 5 በመቅረብ በጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። በማግስቱ ማለትም በ11ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ በ3፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ታሽጎ በዚሁ እለት ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት በአየር አምባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በቢሮ ቁጥር 5 ይከፈታል።
7. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ጠቅላላ ዋጋ ሲቀመጥ ቫትን ያካተተ መሆነ መገለጽ አለበት፡፡
8. በጨረታው አሸናፊ የሆነ አቅራቢ የውል ማስከበሪያ የእቃውን ጠቅላላ ዋጋ 10 በመቶ (10%)በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
9. ት/ቤቱ አሸናፊው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ሳይቀየር 20% መቀነስ ወይም መጨመር ይችላል፡፡

10 አሸናፊው ድርጅት ያሸነፈበትን እቃ ውል ከተፈራረመበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ እስከ ት/ቤቱ ንብረት ክፍል በራሱ ትራንስፖርት ማድረስ ይኖርበታል፡፡

11. ት/ቤቱ በጨረታው የተሻለ ዘዴ ወይም አማራጭ ካገኘ ጨረታውን መሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
12. በማስታወቂያው ላይ ያልተገለጹ ነገሮች ቢኖሩም በግዥ መመሪያው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አድራሻ፡- በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ቦሌ ሚካኤል ሩዋንዳ ኤምባሲ ጀርባ 500 ሜትር ገባ ብሎ**

**ለበለጠ መረጃ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ውስጥ ዘውትር በስራ ሰዓት**

**በስልክ ቁጥር፡-- 011-6262281 /011-8690903/0911939504 ላይ በመደወል መጠየቅ ይችላሉ።**

# የአየር አምባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት